
# ናይል



Nile 7th year; publication No.8, June,2021 ናይል 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 8፣ ሰኔ 2013 ዓ.ም



አቀፍ ግንኙነት መምህርና የህዳሴ ግድብ ተደራዳሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ በባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበብ ህንፃ ለተሳታፊዎች ጥናት ሲያቀርቡ

## የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ አስመልክቶ ሀገራቀፍ አውደጥናት ተካሄደ

በሙሉጌታ ዘለቀ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የብሉናይል ውሃ ተቋም አዘጋጅነት "ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ገፀ-በረከት ለዘላቂ ቀጠናዊ ትብብር" በሚል ርዕስ በጥበብ ሕንፃ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሰኔ 11/2013 ዓ.ም ሀገራቀፍ አውደጥናት ተካሂዷል::

በአውደጥናቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና የህዳሴ ግድብ ተደራዳሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ " Overcoming the Deficit of Trans boundary Water Governance: The case of Northeastern Africa " ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር ጥጋብ በዜ "Historical relationships between the Nile Co-Riparian states (Ethiopia ,Sudan and Egypt): Past Present " እንዲሁም አቶ ፈቂ አህመድ ነጋሽ "Trans-boundary rivers management, global experiences, Ethiopian policies and the challenges in the Blue Nile " ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር አሰግደው ጋሻው እና ውብእግዜር ፈረድ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር ቴዎድሮስ ነጋሽ የግድቡን ቴክኒካዊ ክፍልና እና የሚያመጣውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በተመለከታ ጥናታዊ ፁሁፎችን ያቀረቡ ሲሆን በተሳታፊዎች ጠንከር ያለ ውይይትና ክርክር ተደርጎባቸዋል::

በተጨማሪም ዶ/ር አብረሃ አዱኛ የኢፌድሪ የውሃ ፣መስኖና ኢነርጂ ሚኒስትር ዴኤታ "የታላቁ የህዳሴ ግድብ አስመልክቶ በቀጠናው ያለውን መረጋጋትና በጋራ የመልማት ሀሳብ

ወደ ገፅ 3 ዞሯል




### በውስጥ ገፆች

4 "ለአይነ ስውራን ላፕቶፕ(Laptop)መስጠት ...
11 ስለ "እያሌው ሞኙ በጥቂቱ...
7 ከፍተኛ ትምህርት...
8 ስሜትና ወሬት እስከ የት?
9 ቱና ወጊ ተግባር በተማሪዎቹ
15 "ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ..."




# ናይል

በኢንፎርሜሽን እና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
በውስጥ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ክፍል የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ

ትዕግስት ዳዊት

**ፎቶግራፈሮች**

ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ

**አምደኞች**

ደስታ ተከስተ
አስራት ደርብ
አይንእንግዳ አዳሙ

**አርታኢ**

አቶ ሀሰን ኡስማን

**መልእክተኛ**

መልሸው አጥናፋ
የመረጃ ዴስክ ባለሙያዎች

**ፀሀፊ**

መልሰው አደመ
አበበ ካሳው

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ

**አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ**
**ሰኔ 2013 ዓ.ም**

Contact us:-

https://www.bdu.edu.et

http://www.twitter.com/bdueduet

https://www.facebook.com/bduethiopia

http://www.linkedin.com/school/bahir-dar-university

+251583209653

# ርዕሰ-አንቀጽ

## አረንጓዴ አሻራዬን አስቀምጣለሁ! ግድቤንም ከደለል እከላከላለሁ!

በሀገራችን በመንግስት በዕቅድ ከሚመሩ የልማት መርሃ-ግብሮች በቀደምትነቱ የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ግድቡ በሁሉም የማህበረሰብ ተሳትፎና ከአገር ውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አስተዋጽኦ አሁን ከደረሰበት ደረጃ በመድረሱ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ክብር እና በራስ መተማመን መንፈስ አድሮብናል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ ግድብ በገንዘብና በልዩ ልዩ ድጋፎች የደረሰበት ደረጃ የሚደነቅ ሆኖ በታቀደለት አግባብ እንዲያገለግለን ምሁራን በየሰለጠንበት ሙያ የበኩላችን አስተዋፆ ማድረግ እንዳለብን መዘንጋት የለብንም፡፡

ግድቡን ተከትሎ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር በታቀደ መልኩ በሁሉም ማህበረሰብ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር ተጀምሮ ዘንድሮ ሶስተኛው ዙር የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር የሚካሄድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም ሀገራችን በአለም ታሪክ በአንድ ቀን ሚሊዮኖችን ችግኞች በመትከል ቀዳሚ ብቻ ሳትሆን ግድቡንም ከደለል ለመታደግ ሁሉም ልጆቿ እና ተቋሞች እጅግ አመርቂ ሥራ ሰርተዋል፡፡ ሊመሰገኑም ይገባል፡፡

በአማራ ክልል የሚገኙ አስር ዩኒቨርሲቲዎች ተቀናጅተው ፕሮጀክቶች በመንደፍ ከጣና እስከ ህዳሴው ግድብ ጠንከር ያሉ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራዎች በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡

በአማራ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲወች የሚያደርጉትን የዘንድሮ ጭግኝ ተከላ መርሀ ግብር የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ያዘጋጃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ እና የምርምር አገልግሎት ዘርፍ ከዩኒቨርሲቲው የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጅክ ኮሚኒኬሽን ቢሮ ጋር በመተባበር ይህን የአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር በቀዳሚነት ያስተባብራል፡፡

ስለሆነም የዩኒቨርሲቲው መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ለዚህ መርሃ-ግብር ስኬት መሳካትና በመርሃ-ግብሩ ለመሳተፍ በሚመጡ እንግዳ አቀባበል መስተንግዶ ብሎም ሁለንተናዊ ድጋፍ በማድረግ ተቋማችን የተጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ እንዲወጣ የበኩላችሁን አስተዋፆ እንድታደርጉ የሚለው የናይል የዚህ ወር መልክት መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

## የታላቁ ህዳሴ ግድብ... ከገፅ 1 የቀጠለ

ምን ይመስላል" በሚል ርዕስ ፁሁፍና የአውደጥናቱን ጭብጥ አስመልክቶ ቁልፍ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡


በጥናታዊ ፁሁፎች ላይ እንደቀረበው አሁንም በግብፅ በኩል እየተደረገ ያለውን የሀገራችንን ጥቅምና ሉዓላዊነትን በተዳፈረ መልኩ በአባይ ውሀ ተጠቃሚ የመሆን ሀሳብ በአግባቡ በመረዳት በመንግስት በኩል እየተወሰዱ ያሉ ዲፕሎማሲያዊ ተግባራትን በትክክል በመረዳትና የሀገርን ጥቅም ባስቀደመ መልኩ መስራት እንደሚገባ ተጠቅሷል፡፡

ግብፅ በምትሰጠን ውስጣችንን የመበጥበጥ አጀንዳ ሳንረበሽ መንግስት ይህን ግዙፍ ፕሮጀክት ለመጨረስ ያለውን ቁርጠኝነት እንዲሁም ከታችኛው የተፋሰሱ ሀገራት ጋር በሚደረገው ድርድር የሀገራችንን ጥቅም በሚያስጠበቅ መልኩ ስምምነት እንደሚደረግ በመረዳት የጀመርነውን አጠናቀን ለትውልድ ለማስተላለፍ በአንድነት በመቆም ለአንድ ዓላማ ልንረባረብ እንደሚገባ በአውደጥናቱ ላይ ተጠቁሟል፡፡

አውደጥናቱን በንግግር የከፈቱት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ሙሉነሽ አበበ ካሁን በኋላ ኢትዮጵያ ሀገራችን የራሷ የተፈጥሮ ሀብት ተጠቅማ የመልማት መብቷን ለማረጋገጥ በዲፕሎማሲው መስክ መንግስት ከሚሰራቸው ስራዎች በተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርት ምሁራን፣ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች እና ሞጋች ጋዜጠኞች ከምንጊዜውም በተሸለ መንገድ በጉዳዩ ላይ ጠንክሮ መስራት እንደሚገባ በአፅዕኖት ተናግረዋል፡፡

በአውደጥናቱ የቀረቡትን የምርምር ፁሁፎች የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የብሉናይል ውሃ ተቋም በታዋቂ ጆርናል እንዲሚታተሙ እንደሚያደርግ የተቋሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ዳኛቸው አክሉግ ተናግረዋል፡፡

በአውደጥናቱ ምኒስትሮች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ጥናትና ምርምር አቅራቢዎች፣ ጥሪ የተደረገላቸው ባለሙያዎና ተማሪዎች ታድመውበታል፡፡



የምርምር እና ማ/ሰብ አገልግሎት በያዝነው ዓመት ከ1 ሚሊዮን ችግኞች በላይ እንደሚተከሉ ገለፀ

# ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## “ለአይነ ስውራን ላፕቶፕ(Laptop)መስጠት አይን መስጠት ነው‘’

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አካል ጉዳተኞች ድጋፍና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ልዩ ፍላጎት ያላቸውን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚያግዝ ሰነድ (Guideline) ለመገምገም የግማሽ ቀን አውደ-ጥናት በቤንማስ ሆቴል አካሄደ

በፊት የተቋቋመ ፤ በአማራ ክልል ከሚገኙት 10 ዩኒቨርሲቲዎች ግንባር ቀደም የሆነ የልዩ ፍላጎትን ስራ እያከናወነና ልዩ የኮምፒተር ማዕከል እንዲቋቋም ያደረገ፤በኢኮኖሚ የሚቸገሩትን ማገዝ የቻለ እና ለክፍሉ ስራ አስፈላጊ የሆኑትን የሰው ኃይል ማሟላት መቻሉን አውስተዋል፡፡

እንዲቻል ዳይሬክተሩ አሳስበዋል፡፡

የመርሃ ግብሩን የመግቢያ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የቦርድ አባል ወ/ሮ አስቴር ዘውዱ ለአንድ አይነስውር ተማሪ ላፕቶፕ (Laptop) መስጠት አይን እንደመስጠት መሆኑን ገልፀው የኒቨርሲቲው ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች

ለህፃናት ድርጅት እና ሌሎች ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ሴክተር መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ምሁራን በአውደ ጥናቱ የተገኙ ሲሆን በቀረበው ሰነድ (Guideline) ላይ ሰፊ ማብራሪያና ለግብዓት የሚውሉ ሃሳቦችን ተሰንዝረዋል፡፡

በመርሃ ግብሩ በስራቸው በጎ



የአካል ጉዳተኞች ድጋፍና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ዘላለም ተመስገን ለወርክሾፑ ተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ሲያስተላልፉ

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ አካል ጉዳተኞች ድጋፍና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ዘላለም ተመስገን ጥሪውን አክብረው ለመጡ ታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው የስራ ክፍሉ ከ3 ዓመት

የዓውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ ለልዩ ፍላጎት መብትና ግዴታ ያገለግል ዘንድ የተዘጋጀውን ሰነድ (Guideline) በተለያዩ ምሁራን ለማስገምገምና ከሌሎች ተቋማት ልምድ ለመቅሰም ታልሞ መሆኑን ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩሉን እንዲወጣና የተሻለ ስራ መስራት

አሰልጥኖ ማብቃት ብቻ ሳይሆን ስራ ተቀጥረው እስከሚሰሩበት ሁኔታ ድረስ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጡትን ዶ/ር አለማየሁ ተክለማርያምን ጨምሮ አቶ ታምሩ እሸቴ ከብርሃን

አመለካከት ያላቸውና ለልዩ ፍላጎት ተጠቃሚዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱት ሁለት የአስተዳደር ሰራተኞች ክፍሉ በዩኒቨርሲቲው የዘርፈ ብዙ ዳይሬክተር ዶ/ር ሙሉጎጃም ወንድይፍራው አማካኝነት የምስክር ወረቀት አበርክቶላቸዋል፡፡



የዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች በጥናቱ ውጤት የተገኘውን ቨርሚ ኮምፖስት የተፈጥሮ ማዳበሪያ የጠቀሙ የገበሬዎች የቲማቲም ማሳ ሲጎበኙ

## ችግር ፈች የምርምር ውጤት

በሙሉጌታ ዘለቀ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በጣና ሐይቅ ላይ የተከሰተውን እንቦጭ አረምን ለማጥፋት በተለያዩ ጊዚያቶች በርካታ ሙከራዎችን እና ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱ ይታወሳል; በአሁኑ ሰዓት አረሙ በብዛት በተከሰተበት በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ በቡልቃ አበባ አካባቢ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በስነምድር ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ድግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ተማሪ ታድሎ በላይና ተማሪ ዳኛቸው አየነው የመመረቂያ ፕሮጅክታቸውን የእንቦጭን ብስባሽ፣ የእንቦጭን ቅጠል፣ የእንቦጭን ቅጠልና ግንዱን እንዲሁም የእንቦጩን ስር በማድቀቅ እና በወንፊት በመንፋት እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንቦጩን ወደ አፈርነት ለመቀየት ያስትል ዘንድ ትሎችን ተጠቅመው አራት አይነት ጠጣር ቨርሚ ኮምፖስት/የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲሁም በፈሳሽ መልክ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማዘጋጀት በአርሷ ደሮች ማሳ ላይ የቲማቲም ተክል ሰርቶ ማሳያ ሲያደርጉ ቆይተው በ20/10/2013 ዓ.ም የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገለልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

# ከፍተኛ ትምህርት እና የሰው ሀይል ከገፅ 7 የቀጠለ

ግብዓቶችን የሚያቀርብና ሃብት የሚያፈላልግ ክፍል ነው።

*መዋቅሩ የሚፈልገው የሰው ሃይል:*

ይህ ክፍል የተነቃቃ፣ በየዕለቱ የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎችንና አቀጣጫዎችን ጠንቅቆ የሚረዳ፣ የተረዳውንም ለሰራተኞች በሚመች መልኩ ተንትኖ የሚያቀርብ፣ የሃብት ማፈላለግ፣ ፕሮጀክቶችን የመሳብና ተወዳድሮ የማሸነፍ ችሎታ የመሳሰሉ ባህርያትን የያዙ ሰዎችን ይፈልጋል።

ይህን መዋቅር ወደ ዩኒቨርሲቲዎቻችን መልሰን ስናየው በዚህ መዋቅር ላይ የተፈረጁ የዩኒቨርስቲዎቻችን የሰው ሃይል አደረጃጀቶች ውስጥ የተለያዩ ትምህርት ፋኩልቲዎች ወይም ኮሌጅ ዲኖች ፣ዳይሬክተሮች፣ የምርምር ተቋማት መሪዎችና በተለያዩ የመማር ማስተማርና ምርምር እንዲሁም ማህበረሰብ አገልግሎት ክፍል ውስጥ የሚገኙ አስተባባሪዎች ይገኙበታል።

ይህ ክፍል በዩኒቨርሲቲ እይታ (Perspective) አንጻር ሁለት ባህርያት አሉት። እነዚህ ሁለት ባህርያቶች ደግሞ ዩንቨርስቲ የሚባለውን ተቋም ከሌሎች ተቋማት ይለዩታል።

ምክንያቱም ፋኩልቲዎች በዩኒቨርስቲው ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች (Universities within a University) ተብለው ይጠራሉና። ይህ ማለት ፋኩልቲዎች ራሳቸውን ችለው የዋናውን ዩኒቨርስቲ ባህርያት የተላበሱ ስለሆኑ ነው።

ሲብራራም እያንዳንዱ ፋኩልቲ በራሱ ገለልተኛ ሆኖ እንደ ትምህርት ክፍሉ ሁኔታ የራሱ ተልዕኮዎችና ራዕይ ኑረውት የሚሰራ ክፍል በመሆኑ ነው። በዚህም መሰረት ይህ ክፍል እንደላዕላይ መዋቅር (Strategic Apex) በራሱ የትምህርት ክፍል ባለራዕይ ሆኖ ከላይ በላዕላይ መዋቅር ውስጥ የተዘረዘሩ ባህርያትን እንዲያሟላ ይጠበቅበታል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ አንድ ዩኒቨርስቲ ሲታይ መካከለኛ ደረጃ ላይ በመገኘቱ የዩኒቨርስቲውን ከፍተኛ ክፍልንና የታችኛው ስራ ከዋኝ አካል (Operating Core) አገናኝ ድልድይ ሆኖ ይሰራል። ስለሆነም በዚህ መዋቅር ውስጥ መገኘት ያለበት የሰው ሃይል ከላይ ከዘረዘርናቸው ባህርያት በተጨማሪ በጣም የተነቃቃና ህያው የሆነ የሰው ሃይል (Vibrant and motivated workforce)ይፈልጋል።

ዋና ስራ ከዋኝ ክፍል (Operating Core) : ይህ ክፍል ደግሞ ተልዕኮ ተግባሪ፣ አከናዋኝ ክፍል ነው። እነዚህ ክፍሎች ባጠቃላይ ራዕይን፣ ተልዕኮንና የተለዩ ስልታዊ ጉዳዮችን ሕይወት የሚዘሩ፣ መሬት ላይ የሚያወርዱና የመፈጸም ብቃታቸው ከፍተኛ የሆኑ የተቋሙ ዋና መተንፈሻ ሳንባ ናቸው። እነዚህ ክፍሎች በደንብ ካልተደራጁ ተቋሙ የስሜት ህዋሳቶች እንደ ጎደሉበት ሰው በድንግዝግዝ የሚሄድ ግኡዝ አካል ይሆናል።

*መዋቅሩ የሚፈልገው የሰው ሃይል:* በዚህ መዋቅር ውስጥ እንዲገኝ የሚፈለገው የሰው ሃይል ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል፣ ሩጦ የማይደክም፣ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ በደንብ የተረዳ ለአተገባበሩ የሚተጋ የሰው ሃይል ነው። በተጨማሪም ከየዕለት ተሞክሮ ራሱን የሚያስተምር አዳዲስ አሰራሮች እንዲኖሩ ሃሳብ የሚያመነጭ እንዲሆን ይጠበቃል።

ይህን መዋቅር ወደ ዩኒቨርሲቲዎቻችን መልሰን ስናየው በዚህ ቦታ ላይ ከሚገኙ የሰው ሃይል መዋቅር ውስጥ በተለያየ የሙያ እርከን የሚገኙ መምህራን ፣ተመራማሪዎችን፣ በመማር ማስተማርና በምርምር ሂደት ውስጥ እገዛ የሚያደርጉ የተለያዩ ቴክኒሺያኖች፣ ወዘተ የሚገኙበት ክፍል ነው።


እንግዲህ ከላይ በሄነሪ ሚንትዝበርግ የተቋማት መዋቅር ስዕላዊ ገለጻ መሰረት ከላይኛው እርከን (Strategic Apex) እስከ ታችኛው እርከን (Operating Core) ድረስ ያለው መዋቅር ሶስቱንም ክፍሎች በአንድ የዕዝ ሰንሰለት ውስጥ አስገብቶ ይገኛል። ከላዕላይ መዋቅር ውስጥ የዩኒቨርስቲ ቦርዶችን ብናወጣቸው ሌሎች ሰዎች በመማር ማስተማርና በምርምሩ ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ በመሆናቸው መምህራን (Academic Staff) ብለን እንጠራቸዋለን።

በዚህም መሰረት ይህ የመዋቅር ክፍል የዩኒቨርስቲው ተልዕኮ ማለትም መማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት መፈጸሚያ ክፍል በመሆኑ እዚህ ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች የስራ ባህርያት ልዩነት ፈጣሪ እንዲሆኑ ይጠበቃል። ይህም ማለት በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን በጥሩ ስብዕና የሚቀርጹ፣ ዕውቀታቸውን ለማካፈል የማይሰስቱ፣ ተማሪዎችን ለመርዳት ደከመኝ ሰለቸኝ የማይሉ፣ ሁልግዜም በጊዜ ሰሌዳቸው መሰረት ክፍል ውስጥ ወይም ማስተማሪያ ቦታ የሚገኙ፣ ተማሪዎችን በማማከር በኩል ትጉ የሆኑ አባታዊና እናታዊ ጠባይ ያላቸውና ለተማሪዎቻቸውና ለስራ ባልደረቦቻቸው መልካም አርአያ የሚሆኑ መምህራን እንዲሆኑ ይፈልጋል።

በምርምሩ ረገድ ደግሞ ትጉ ተመራማሪ የሆኑ፣ ተልዕኳቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መፍታት የሚችሉ፣ የተለየ እይታና ብሩህ አእምሮ ያላቸው፣ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ከፊት መስመር ላይ የሚገኙ፣ ጥቅመኛ ያልሆኑ፣ ጨለምተኛ አስተሳሰብ የሌላቸው፣ በአመክንዮ የሚያምኑ የጥሩ ስነምግባር እንዲሁም የከፍተኛ ዕውቀትና ችሎታ ባለቤት የሆኑ ሰዎች እንዲኖሩት መዋቅሩ ይፈልጋል። ምክንያቱም መምህራንና ተመራማሪዎች የተቋሙ አስኳል (Core) ናቸውና።

አሁን ደግሞ ከዋናው የዕዝ ሰንሰለት በጎንና ጎን ያሉ ሁለቱን የስራ ክፍሎች ባህርያትንና የሚፈልግባቸውን የሰው ሃይል አሰላለፍ እንመልከት ።

ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች (Supporting Staff): ይህ ክፍል ደግሞ ስልት




ቀያሾች (Strategist) ፣ስልት ተርጓሚዎችና ከዋኞች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ያለምንም እንከንና ችግር በተልዕኮ ፣በግብና በዝርዝር ተግባራት መካከል የተነጣጠለ ስራ ሳይኖር በሰላና ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ስራ እንዲከወን የተለያየ እገዛ ወይም ድጋፍ የሚያደርግ የስራ መዋቅር ነው።

*መዋቅሩ የሚፈልገው የሰው ሃይል:* በዚህ መዋቅር ውስጥ እንዲገኝ የሚፈለገው የሰው ሃይል አጠቃላይ የፋይናንስ፣ የሰው ሃይል፣ የገበያ ጥናት፣ የግዥ ስርዓት አተገባበርና የመንግስትን ፖሊሲዎችና ደንቦችና ጠንቅቆ የሚያውቅ ቀልጣፋ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ የማይል፣ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ በደንብ የተረዳና ለትግበራው የላቀ እገዛ የሚያደርግ፥ የራሱን የስራ ክፍል ተግባር ከተቋሙ ራዕይና ተልዕኮ ጋር አስተሳስሮ የሚሰራ ነው።

ይህን መዋቅር ወደ ዩኒቨርሲቲዎቻችን መልሰን ስናየው በዚህ መዋቅር ውስጥ ለጠቀሱ የሚችሉ የስራ ክፍሎች ውስጥ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የፋይናንስና በጀት ፣የአይሲቲ ፣የግዥ ክፍል ፣ማኔጂንግ ዳሬክተሮች፣ የህንፃ ግንባታና ጥገና ክፍሎችን፥ የተማሪዎች አገልግሎት ወ.ዘ.ተ የሚያካትት ክፍል ነው።

በዚህም መሰረት ይህ የመዋቅር ክፍል የዩኒቨርስቲው የመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ተልዕኮ በብቃትና በጥራት እንዲተገበር ከፍተኛ የሙያ እገዛ የሚያደርግ ክፍል በመሆኑ ቅን፥ ችግር ፈቺና ስራ አሳላጭ፥ የመማር ማስተማሩን፥ የምርምሩንና የማህበረሰብ አገልግሎት ዕቅዶችን የሚረዳና ተፈፃሚነታቸውን ማገዝ የሚችል የላቀ ችሎታ (Superior Skill) ባይርያት ያላቸው የሰው ሃይል አደረጃጀት እንዲኖረው ይጠይቃል።

ቴክኒካል ጉዳዮች ክፍል (Techostructure):- ይህ ክፍል የተቋሙንና አካባቢውን በመመልከት ትንተና የሚሰጡ ሁነት ተንታኞች (Analysts) ናቸው። የተቋሙን ስልታዊ ዕቅድ የሚያዘጋጁ ፣ የተልዕኮ አፈፃፀም ጥራትን የሚቆጣጠሩና የሚለኩ፥ የተቋሙን ሀቅም መገንባት የሚችሉና የስራ ኦዲት ማድረግ የሚያስችል ልዩ ልዩ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው የልዩ ባለሙያዎች ስብስብ ክፍል ነው ።

*መዋቅሩ የሚፈልገው የሰው ሃይል:* በዚህ መዋቅር ውስጥ እንዲገኝ የሚፈለገው የሰው ሃይል አጠቃላይ መረጃዎችን በጥልቀት ማየትና መረጃዎችን ማደራጀት፥ መቀመርና መተንተን የሚችል፥ ሁኔታዎችን በማገናብ ለውሳኔ ሰጭ አካላት የመፍትሄ ሃሳብ ማመንጨት የሚችል፥ ቴክኒካል ጉዳዮች ላይ የላቀ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው፥ የሁኔታ ትንተና ክህሎት ያላቸው፥ የተለያዩ የሀቅም ማጎልበቻ ስልቶችን የሚቀይስና ክፍተት የሚሞላ ብቃት ያለው የሰው ሃይል አደረጃጀት እንዲኖረው ይፈለጋል።

ይህን መዋቅር ወደ ዩኒቨርሲቲዎቻችን መልሰን ስናየው በዚህ ቦታ ላይ የሚገኙ የስራ ክፍሎች ለምሳሌ ያክል የሀቅም ግንባታ ክፍል፥ የስልታዊ ዕቅድ (Stategic Planning) ቡድን፥ የጥራት ማረጋገጫ ( Quality Audit)ክፍል፥ ኦዲተሮች፥ የዩኒቨርስቲውን ላዕላይ መዋቅር ያሉ የስራ ሃላፊዎችን በተለያየ ጉዳይ የሚያማክሩ አማካሪዎችን፣ወዘተ ያጠቃልላል።

ውድ አንባብያን:- በሚቀጥለው መጣጥፌ እነዚህ አምስቱን ተቋማዊ መዋቅሮች በሁለት ዘርፎች በመሰብሰብ ማለትም መምህራ (Academic )ና የአስተዳደር ሰራተኞች (Administrative staff) በማለት የባህር ዳር ዩኒቨርስቲን አሁናዊ ሁኔታ ከራዕዩና ከተልዕኮው ጋር በማጣመር በመረጃ ላይ ተመስርቼ ትንታኔ አቀርባለሁ።

ይቆየን!

# መሪነት እና የኃይል አጠቃቀም ከገፅ 14 የቀጠለ

አለህ ማለት ነው::

ስለዚህ ይህን የኃይል አይነት የመረጃ እና ማስረጃ ኃይል ልንለው እንችላለን። ምንጩ ግለሰባዊም ሥልጣናዊም ሊሆን ይችላል።

ለመረጃዎች ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ትጉህ እና መረጃ አነፍናፊ ሰው አለ። የመረጃ ምንጮችን ሁሉ ማሰስ እና መዳሰስ የሚችል እና ጠቃሚ መረጃዎችን ማጠናቀር እና መሰነድ የሚችል ሰው የመረጃ ኃይል ይኖረዋል። ነገር ግን ደግሞ አንድ መሪ በሥልጣን ወንበር ላይ ሲቀመጥ ከብዙ አካላት (ከሠራተኞች፣ የበላይ አለቆች፣ ከተመሳሳይ ድርጅት ተወካዮች፣ ከደንበኞች፣ ከመንግሥት አካላት ወዘተ) ጋር ግንኙነትና ትስስር ስላለውና ይህን ትስስር እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ በራስ ጥረት መረጃ የማግኘት ቅድምና (Privileges) ስላለው እንዲሁም ደግሞ በትስስሩ መሠረት የመረጃ ፍሰቶች እና ልውውጦች ሲለሚኖሩ የመረጃ ማስረጃ ኃይልን ለማግኘት ሥልጣን በሚገባ ያግዛል። ስለዚህ የዚህ ኃይል ምንጩ ሁለቱም ናቸው ሊባል ይችላል።

**ረ. የትስስርኃይል(Power of Connection/link)፡**

ከባለሥልጣኖች ጋር፣ ከባለሀብቶች ጋር እንዲሁም ከማንኛውም ኃይል ካላቸው (ተጽእኖ ፈጣሪዎች) ጋር ባላቸው ትስስር (የዝምድና፣ የትውውቅ፣ የሽርክና እና አብሮ መሥራት ወይም ሌሎች ልዩ ልዩ) ኃይልን ገንዘብ የሚያደርጉ ሰዎች ይኖራሉ።

እነዚህ ሰዎች "ምን ታውቃለህ ሳይሆን ማንን ታውቃለህ" የሚለው ጥያቄ ቀላል የሚሆንላቸው ልንላቸው እንችላለን። የሚፈልጉትን ነገር ለማስፈጸም ትስስራቸውን እንደ መርጃ መሳሪያም ሆነ ማስፈራሪያ የሚጠቀሙ ማለትነው።

**ሰ.ሌሎች** ተጠቃሽ የኃይል አይነቶችም አሉ፡ለምሳሌ **የገንዘብኃይልን(Power of Money or Wealth)** ማንሳት ይቻላል። ሀገሬውም ሲተርት "ሀብት ካለ በሰማይ መንገድ አለ" ይላል። ገንዘባቸውን ተጠቅመው የፈለጉትን የሚያስፈጽሙ እና ተጽእኖ የሚያደርጉትን የገንዘብ ኃይል አላቸው ሊባል ይችላል።

እንደየአካባቢውና እንደየባህሉ የሚለያዩ ሌሎች የኃይል አይነቶችም አሉ። ለምሳሌ፡-በተለይ በእኛ ሐገር ከወጣቶች ይልቅ ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች የበለጠ ተሰሚነት እና ተአማኒነት አላቸው። ይህንን ተጠቅመው ሥራ መሥራትና ለውጥ ማምጣት ይችላሉ፤ ይህም እንደ አንድ ኃይል ሊወሰድ ይችላል። ይህንንም ስም እንስጠው ከተባለ **የእድሜ ኃይል(Power of Age) እና የእምነት ኃይል(Power of Belief)** ብለን ልንሰይመው እንችላለን።

በሌላ በኩል ደግሞ ከሴቶች ይልቅ ወንዶች በሐገራችን ባህል (ምንም እንኳን እንደአካባቢውና እንደየሁኔታው ቢለያይም እና ወጥ የሆነ አሳማኝ ጥናት ባይኖርም) የበለጠ የውሳኔ ሰጭነት ሚና እና ቅቡልነት አላቸው የሚለው በብዙሀኑ ዘንድ ተቀባይነት ያለው አስተያየት አለ። በአባባሉም " ምን ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" ይባላል::

ይህ አስተሳሰብ እና አፈጻጸሙ እስከ ዘመናችን የነበረውን የሚያጠቃልል ሲሆን አሁን ላይ ሴቶችን የማብቃት እና የማበረታታት በርእዮተ-ዓለም፣ በፖሊሲ እና ህጎች ጭምር የታገዘ ዘመቻ ስላለ ወደፊት ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ተሰሚዎች፣ ተጽእኖ ፈጣሪዎች እና ውሳኔ ሰጭዎች የማይሆኑበት ምክንያት አይኖርም። ስለዚህም በተናጠል ስናየው **የወንዴነት(ተባእታይ) ኃይል እና የሴቴነት (አንስታይ) ኃይል ወይም በጥቅሉ የጾታኃይል (Power of Sex or Gender Power)** ልንለው እንችላለን:: ምንጩ ፆታና ለፆታ የተሰጠው ሚና ነውና።

የኃይል ምንጭን በተመለከተ መነሳት ያለበት ሌላው ጉዳይ፣ አንድሰው/መሪ ከእራሱ ጥረት እና በተፈጥሮ ከተቸረው ስጦታ እንዲሁም በሥልጣን ከሚያገኘው ኃይል በተጨማሪ የማኅበረሰቡ አስተዋጽኦ ነው። መሪው አንድን የኃይል አይነት እንዲጎናጸፍ በማኅበረሰቡ ሁለንተናዊ ድጋፍ እና ጥረት(Societal Support and Effort) ይታገዛል። ይህም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የመሪውን ማንነት በመገንባትና ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንዲሁም መሪው የሚመራበትን ማዕቀፈ እሳቤ በመቅረጽ ሊገለጽ ይችላል። ስለዚህ የኃይል ምንጮቹ ልዩ ልዩ እና የተሳሰሩ ናቸው።

## የኃይል አጠቃቀም መርሆዎች

ኃይል መኖሩ በራሱ በቂ አይደለም፡ ፡ አንድ መሪ ውጤታማ እንዲሆን እና ለውጥ እንዲያስመዘግብ ከፈለገ የኃይል አጠቃቀም መርሆዎችን በሚገባ መረዳት አለበት። ስለኃይል አጠቃቀም እንደ መርሆ ሊቆጠሩ የሚችሉና መሪዎች ሊገነዘቧቸውና ሊከተሏቸው የሚያስፈልጉ ለውጤታማነት የሚያበቁ ምክሮችን ለመጠቆም ያክል የሚከተሉትን ማለት ይቻላል።

1. **ኃይልን ወደ ተጽእኖ መፍጠር(Influence) መቀየር፡** ፡መሪዎች ኃይልን ገንዘብ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ኃይላቸውን በሂደት ተከታዮችን ለማሳመን፣ ለማበረታታት፣ ለማነሳሳት፣ ለመወሰን፣ ለመሸለም፣ ለመቅጣት ወዘተ በአጠቃላይ ሥራ ለማሰራት መጠቀም አለባቸው። ይህም ተጽእኖ መፍጠር ይባላል። ይህም የመሪነት አስኳል/ልብ (Nucleus) ነው ይባላል። ይህን ሲያደርጉ ኃይላቸውን ተጠቀሙ(Exercising of Power) እንላለን። ይህ ተጽእኖ መፍጠር ይሁንኝ ተብሎ የሚተገበር (Deliberate and Intentional) ተግባር መሆን አለበት:: ማለትም ግብ ተኮር መሆን አለበት::

ኃይል የምንጠቀመው የሆነ አላማ ለማሳካት መሆን አለበት። እንዲሁ በዘፈቀደ እና በአጋጣሚ የሚፈጠር ተጽዕኖ ወደ መሪነት አያደርስም።ኃይል ቋሚ ንብረት ሳይሆን የሚገኝና የሚለማ እንዲሁም የሚወሰድና የሚጠፋ መሆንን ተገንዝቦ መንከባከብ፣ ማሳደግ እና ወደሥራ ማዋል ወይም መጠቀም ያስፈልጋል።

ያለዚያ ቅቡልነትም ይሁን ተጠቃሽነት፣ መቅጣትም ይሁን የትስስር ኃይል ሁሉም ሊጠፉ ወይም ሊወሰዱ እና ብንፈልግ እንኳን መጠቀም የማንችላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በተለይ በሥልጣን የሚገኝ ኃይል የሥልጣን ዘመን ሲያበቃ አብሮ የሚቀር ይሆናል።

2. **ለስላሳ ኃይል መጠቀም፡** ብልህ እና ውጤታማ መሪዎች በአመዛኙ ቅጣት ላይ ካተኮረ ኃይል (coercive power) ይልቅ ማሳመንን፣ ማበረታታትን እና ማነሳሳትን መሠረተ ላደረገ ስላሳኃይል (non-coercive or soft power) አጠቃቀም ያደላሉ።

የሚሻለውም ይኸው እንደ ሆነ የዘርፉ ምሁራን ይስማማሉ። ይህ ማለት ግን ቅጣታዊ ኃይልን መጠቀም አያስፈልግም ማለት አይደለም።

3. **የኃይል ምንጫቸው ምን እንደሆነ መረዳት፡** በግለሰባዊ ማንነታቸው የሚመጣውን እና ከሥልጣናቸው የሚገኘውን ኃይል መለየት አለባቸው።ምክንያቱም ሁለቱን በአንድ አይነት ሁኔታ በተመሳሳይ መንገድ መጠቀም ስለማይቻል ነው።

4. **የተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ የተለያዩ የኃይል አማራጮችን መጠቀም፡**ለአንድ ነባራዊ ሁኔታ ሁሉንም አይነት ኃይሎች እኩል ሊያገለግሉ አይችሉም ወይም ደግሞ ሁሉም ኃይሎች ለተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎች እንደ አማራጭ ኃይል አይቀርቡም። ይሁንእንጅ ልዩ ልዩ ኃይሎች ተፈላጊ የሚሆኑበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ስለዚህ መሪዎች ለምን አይነት ሁኔታ የትኛውን አይነት ኃይል መጠቀም እንዳለባቸው መገንዘብና ነባራዊ ሁኔታውን ግምት ውስጥ ያስገባ የኃይል አጠቃቀም(situational or contingent to the situation) ሊተገብሩ ይገባል። እውቀት በሚያስፈልግበት ሁኔታ ጉልበት ወይም ስልጣን ቢጠቀሙ ነገር ይበላሻል።

5. **ብዙ አይነት የኃይል አማራጮችን አቀናጅቶ መጠቀም፡**

አንድ መሪ ብዙ የኃይል አይነቶች ቢኖሩት እና እነሱን እያቀናጀ እንደየ አገባቡ ቢጠቀም ይመረጣል። መሪው ሥልጣን ብቻ ከሆነ ያለው ሌሎች የኃይል አይነቶችን ለማካበት እና ለማጎልበት መጣር አለበት። ይህም አንድ መሪ ከሚጠበቅበት አላባዎች አንዱ የሆነው ራስን የማብቃት (Self Development) ተግባራት አካል መሆን አለበት::

ስለዚህ ብዙ የኃይል አይነቶችን ማዳበርና አንዱን ከሌላው አቀናጅቶ (ቢቻልብዙአይነትኃይላትን) መጠቀም ያስፈልጋል። የመቅጣትን ወይም የመሸለምን ኃይል ብቻ ሁሌም ቢተገብረው ውጤታማ ላይሆን ይችላል።

ስናቀናጅም "ሲቻል በውዴታ ሳይቻል በግዴታ" አይነት የማናለብኝነት ኃይል ማፈራረቅ ሳይሆን ልዩ ልዩ ስልታዊ የኃይል ቅንጅት መንገዶችን በመጠቀም መሆን አለበት።

ከፈጻሚ ለውጤታማነት የሚያበቃ ግዳጅ ይፈጽማሉ ተብሎ ይታመናል።

# እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

# ከፍተኛ ትምህርትና የሰው ሃይል (Higher Education and Workforce)

በአስራት ደርብ
PhD candidate in Higher Education Leadership and Management
Email: asrat.dereb@bdu.edu.et, or asd.dereb5@gmail.com

ቅድም ሃሳብ፡- በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በተከታታይ ስለከፍተኛ ትምህርት ምንነት፣ እድገት፣ ተልዕኮ በአጠቃላይ የሴክተሩን አስተዳደርና አመራር ጥበብ በፅንሰ ሃሳብና በተግባር ምርምር የተደገፈ ፅሁፍ አቀርባለሁ:: ውድ አንባብያን በማቀርበው ሃሳብ ላይ አስተያየት፣ጥያቄ፣ ተቃርኖአዊ ሃሳብ ካላችሁ ከላይ ባስቀመጥኩት ኢሜል ሃሳባችሁን መላክ ትችላላችሁ:: ፅሁፎቼ ሃሳቤን በደንብ ይገልፅልኛል ብየ ባመንኩበትና ተድራሽነቱን በደንብ በለየሁበት አግባብ በአማርኛም በእንግሊዘኛም ቀያይጬም ሆነ በተናጥል እንደማቀርብ ከወዲሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ::

(አንዳንድ ከእንግሊአዝኛ ወደ አማርኛ የተተረጎሙ ቃላት ውርስ ትርጉም እንጂ በመደበኛ መዝገበ ቃላት የተገኙ አይደሉም::)

በባለፈው ጽሁፌ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ የሆነውን መካነ አእምሮ ወይንም ዩኒቨርስቲ ትምህርት ቤት በሚለው አተያይ (Perspective) ምን መምሰል እንዳለበት መነሻ ሀሳብ ማቅረቤን ለማስታወስ እወዳለሁ::

ይህንንም ያደረግሁበት ምክንያት በዩኒቨርስቲው ውስጥ ያለውን ዝርዝር ጉዳዮች በጥልቀት ገብቼ ከማየቴ በፊት ተቋሙ የሚቆምበትንና የቆመበትን መደላድሉን ማበጀት የአንድ ህንፃ አናጭ ቁልፉ ስራው ስለሆነ እኔም ውስጥ ያሉ ዝርዝር ጉዳዮችን በአትኩሮት ከማየቴ በፊት ዋና መሰረቱ (Foundation) ላይ ማተኮር በመፈለጌ ነው::

በዩኒቨርስቲ ውስጥ የሚገኙ አጋር አካላት በተለይም ደግሞ የስራ መሪዎች ስራ መስራት ከመጀመራቸው በፊት ስራ የሚሰራበትን አስቻይ ከባቢ (Enabling Environment) በጥንቃቄ ማበጀት ስላለባቸው በተቋሙ ውስጥ መሰራት ያለባቸው ሁለት ቁልፍ ነገሮችን አንስተናል:: አንድ ተቋም በግርድፍ እይታ የሁለት ነገር ውጤት ነው ብለናል፤እነሱም ፊዚካዊ አካባቢ ስሬት (Physical Environment Makeup)ና የስነ ልቡናዊ ስሬት (Psychological Makeup) በመሆናቸው ናቸው::


እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ላይ በጥንቃቄ ሰርቶ መደላድሉን ያሳመረ ተቋም ሌሎች ተግባራት ላይ የሚያወጣው ጉልበትና ሃብት በቀላሉ ሊያሳልጥለትና ጥሩ ውጤትም ሊያስመዘግብ ይችላል::

ስለሆነም በዚህ ፅሁፍ ለአንድ ተቋም ስኬትም ሆነ ውድቀት ወሳኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል የዩኒቨርሲቲው የሰው ሀይል ዋናና ቀዳሚው ስለሆነ የዩኒቨርስቲዎች የሰው ሀይል አሰላለፍና አሰራር እንዲሁም አመራር ላይ በጽንሰ ሃሳብና በተግባር ላይ የተመሰረተ ሃሳብ ማንሳት ወደድሁ::

## ዩኒቨርሲቲና የሰው ሀብት ግርድፍ እይታ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ፈርጀ ብዙ ተልዕኮዎች ያሉት ተቋም ከመሆኑ አንጻር የተቋሙ አደረጃጀትና በአደረጃጀቱ ውስጥ የሚኖረው የሰው ሃይል በተለየ እይታና በልዩ ጥንቃቄ መታየት ይኖርበታል:: ምክንያቱም ተቋሙ የትምህርት፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት የሚሰጥበት፤ እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቁ ባለሙያዎች፣ ተመራማሪዎች የሚፈሩበት ተቋም ነው:: ስለሆነም በተቋማት ልየታ ስርዓት ውስጥ ዩኒቨርስቲዎች በከፍተኛ ሙያዊ ተኮር ተቋማት (Highly professional oriented organization) ውስጥ ይመደባሉ::

ስለዚህ የዛሬ መጣጥፌን የሄነሪ ሜንትዝበርግ "የተቋማት አወቃቀር" ጽንሰ ሃሳብ መነሻ በማድረግ በእያንዳንዱ አወቃቀር ውስጥ መኖር ያለበትን የሰው ሃይል ላይ ብቻ አተኩሬ አቀርባለሁ::




ሜንትዝበርግ የተቋማትን የአሰራር ስርዓት ዝርጋታን በተመለከተ በስዕሉ ላይ እንደሚታየው በአምስት መዋቅራዊ ክፍሎች ይከፍላቸዋል:: እነዚህን ክፍሎች ከዩኒቨርስቲዎች አሰራር አንጻር አንድ በአንድ እየቃኘን እንመልከታቸው::

### ላዕላይ መዋቅር (Strategic Apex):-

ይህ የመዋቅር ክፍል የተቋሙ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የሚዘወርበት፣ ስልታዊ ሃሳቦች የሚውጠነጠኑበት፣ የተቋሙ መጻኢ እድል የሚወሰንበት፣ አቅጣጫ የሚሰጥበትና ተቋሙን ከውጭው ዓለም የሚያስተሳስር ዋና ክፍል ነው::

መዋቅሩ የሚፈልገው የሰው ሃይል፡

ይህ መዋቅር ከፍተኛ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች የሚፈልግ፣ ጠንካራ አደረጃጀት የሚሻና የተነቃቃ የሰው ሃይል አሰላለፍ የሚጠይቅ ቦታ ነው:: በዚህ መዋቅር ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ሊኖራቸው ከሚፈለገው የስራ ባህርያት መካከል ዋና ዋናዎችን ለመጥቀስ ያክል ባለራእይ፣አርቆ አላሚነት፣ የውጭውን አካባቢ ተለዋዋጭ ባህርይ መገንዘብ የሚችሉና እንደ ሁኔታው የተለያዩ ስልቶችን መቀየስ የሚችል አእምሮና አስተሳሰብ ያላቸው፣ ሃላፊነትን መውሰድ የሚችሉ (Risk Taking) ና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፈጣን ውሳኔ ሰጭነትና ብሩህ አእምሮ (Open minded) ባህርያትን የተጎናጸፉ ሰዎችን የሚፈልግ ቦታ ነው::

ከላይ የተዘረዘረውን ሃሳብ ወደ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ስንመልሰው በዚህ መዋቅር ላይ ከሚገኙ ቁልፍ የሰው ሃይል አደረጃጀቶች ውስጥ የዩኒቨርሲቲዎች ቦርድ ፣ ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ የማኔጅመት አባላት ወ.ዘ.ተ ናቸው::

እነዚህ ሰዎች በመሰረታዊ የዩኒቨርስቲው ቁልፍ ጉዳዮች (Strategic Issues) ላይ ውሳኔ የሚያሳልፉ፣ የዘወትር ስራዎቻቸው ስልታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር፣ ዩኒቨርስቲውንወደፊት የሚያስፈነጥሩ፣ መርህ አደር፣ አቅጣጫ ጠቋሚና ባለራዕይ ሰዎች የተሰባሰቡበት ክፍል እንዲሆን ይፈለጋል::

ዩኒቨርስቲዎቻችን የዕውቀት መፍለቂያና የምርምር ተቋማት በመሆናቸው ይህ የመዋቅር ክፍል የሚጫወተው ሚና ትልቅ ነው:: ወደዚህ ክፍል የሚመጡ ሰዎች ከመሪነት ባህርይ ጋር ቁርኝት ያላቸው በመሆኑ ስልታዊ አመራርን(Strategic leadership) እንደ መርህ ቢጠቀሙ አትራፊ እንደሚሆኑ ምክረ ሃሳቦች አሉ:: ይህ ግን የሚሆነው የተቋሙን ነባራዊ ሁኔታ በማንበብ ነው:: ይህም ማለት የተቋሙ ታችኛው መዋቅር ላይ ያሉ አመራሮችና ሰራተኞች የስራ ላይ አፈጻጸም ብቃትና ተልዕኮን የመሸከም ጥንካሬያቸው በደንብ ተጠንቶና ተተንትኖ መረጋገጥ ሲቻል ነው:: ወይም ደግሞ ከዚህ መዋቅር በታች ያለውን ክፍል የማስፈጸምና የመፈጸም ሃቅሙን በማላቅ (Empowering)፣ የስራ ነጻነት በመስጠት (Granting Autonomy)ና የስራ እምነትን በመገንባት (Building trust) የሰው ሃይል ማደራጀት ሲቻል ስልታዊ አመራርን መተግበር ይቻላል::

በእርግጥ የዚህ ጽሁፍ አላማ መዋቅሩ የሚፈልጋቸውን የሰው ሃይል ባህርያትን ማሳየት በመሆኑ በዚህ ክፍል ውስጥ ሊኖር የሚገቡ የአመራር ጥበብ በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ::

### መካከለኛው መዋቅር (Middle Line): -

ይህክፍልከላይኛውመዋቅርየሚወጡ ፖሊሲዎችን፣መመሪያዎችን፣ አቅጣጫዎችን ቅርጽ ይዘው ተተንትነውና ተተርጉመው እንደስራ ክፍሎቹ ሁኔታ ወደ መሬት እንዲወርድና ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚያሳልጥና መደላድል ሰሪ ክፍል ነው:: ይህ ክፍል የታችኛውንና የላይኛውን መዋቅር ድልድይ ሆኖ የሚያገናኝ ሲሆን በተጨማሪም ለፖሊሲ አፈጻጸም እገዛ የሚያደርጉ

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

# ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

## ስሜትና ወረት እስከ የት?

በደስታ ተከስተ
ባ/ዳር ዩኒቨርስቲ ict ክፍል

በአንድ ወቅት ላይ የኢትዮጵያ አትሌትክስ ቡድን በዓለም አደባባይ እጅግ ደማቅ ታሪክ አስመዝግበዉ ነበር በዚያን ሰሞን ታድያ በርካታ ዜጎች ሀገራዊ ስሜታቸዉ ተነሳስቶ እንደ ነበር አስታዉሳለሁ በግዜዉ ብዙ ሰዎች ማለዳ ማለዳ እየተነሱ በየአዉራ ጎዳናዎች ላይ መሮጥ ጀምረዋል ነበር፡እንዴት ነዉ፡ሲባሉ፡ እኔም ነገ በዓለም መድረክ ተሳትፌ የራሴንና የሀገሬን ስም በበጎ አስጠራለሁ በማለት ምኞታቸዉን ሲገልጡ ተሰምተዋል፡፡ዉለዉ ሳያድሩ ግን ጠዋት ጠዋት በሯጮች ተሞልተዉ የነበሩት የከተማ መንገዶች እንደተለመደዉ ጭር ማለታቸዉን ቀጠሉ ..ስሜትና ምኞት እየቀሰቀሰ ሲያስሮጥ የነበረዉ ሰሞነኛ ክስተት ወረቱ አልቆ ነበርና ነዉ፡፡

አንዳንድ ግዜ በሆነ ስሜት ስንነካ ሰዋዊ ሞራላችን ጣሪያ ይደርስና በምኞት ፈረስ እየጋለብን ..ማይነካዉን ለመንካት የማይደረስበትን ለመድረስ በከንቱ ስንዳክር የምንስተዋል ብዙዎች ነን ግዚአዊ ስሞቶቻችንን መቆጣጠር ሲያቅተን ዉሎ አድሮ የምንፀፀትበትን ዉሳኔዎችንና ተግበራትን የፈፀንባቸዉ አጋጣሚዎች ይኖሩ ይሆን? አብከዛኞቻችን በፖለቲካ አመለካከታችን ብንመዘን የስሜት ተቃዋሚዎችና የወረት ደጋፊዎች ሆነን መገኘታችን አይቀርም::

ስንት ግዚአቶች በምክናያታዊነት ሳይሆን በስሜት ምንደግፋቸዉንም ሆነ የምንቃወማቸዉን አካላት ፎቶግራፋቸዉን በቫረንና በአቡጀዲ ጨርቅ ላይ አሰርተን የዘመርላቸዉና የረገምናቸዉ አያሌዎች ይኖራሉ ነገሮች ካለፉ በኂላ ለምን እዳደረግነዉ ስንጠየቅ በቂ የሆነ ማብራሪያ የማንሰጥበት ይልቁንም የምናፍርበት አግጣሚዎች ይበዛሉ::

ይህ እንግዲህ ከጅምሩ በምክንያት ታግዘን በዓላማ ላይ ተመስርተን ነገሩን መከወን አለመቻላችን ይመስለኛል ስመታዊ መሆን ለአደጋ ያጋልጣል ግዚአዊ በሚፈጠር ስሜት ዘላቂ በሆነዉ የህወታችን መስመር ላይ እንቅፋት መፍጠራችን የማይቀር ነዉ ይህ አሉታዊ የሆነ ስሜታችን ከእኛም አልፎ የሌሎች ሰዎችንም ህይወት የሚያናጋ ሌሆንም ይችላል፡፡

የአንድ በቅርበት የማዉቀዉን ሰዉ ሁኔታ ስታዘብ አግራሞትን የሚጭሩብኝ አጋጣሚዎችን አስተዉያለሁ ይህ ሰዉ ፖለቲከኛ ባይሆንም በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሲበዛ ስሜታዊና ተለዋዋጭ ባህሪ ዓይነት ያለዉ ነዉ... በቀደመዉ መንግስት የነበረ ጠ/ሚኒስተር በሞት በተለየበት ወቅት ይህ ሰዉ እጇግ ስሜታዊ ሆኖ ሀዘኑ ቅጥ ያጣ ከእርሱ በላይ ሀዘንተኛ የሌለ እስከማይመስል ድረስ እዩኝ እዩኝ ዓይነት አፋሽ አጎንባሽ አወዳሽ ሆኖ ነበር በግዜዉ በሚከወኑ ቀበሌአዊ ዝግጅቶች ላይ ሁሉ አለሁ አለሁ በማለት አቧራ ማስነሳቱን አስታዉሳለሁ::

ነገሮች አልፈዉ ሁኔታዎች ከተቀየሩ በኂላ ዛሬ ላይ የዛን ግዜ ድርጊቱ በጨዋታ መካከል ሲነሳበት የመሸማቀቅ ስሜት እየተስተዋለበት ትክክል እዳነበረና እደተሸወደም ሲናገር እሰማዋለሁ ግለሰቡ ዛሬም በወቅታዊ ፖለቲካዊ ሁኔታ በስሜት ሰክሮ ይታያል ለሚናገረዉም ሆነ ለሚያደርገዉ ነገር ፍሬአዊ ምክናያት ሲያቀርብ አይታይም ይህ እንግዲህ ግለሰባዊ ምልከታ ሊሆን ይችላል ሰፊ የሆነ ጥናት ቢደረግበት ማህበረሰባዊ ጉድለት ሊሆን ይላል የሚል ግምታዊ ሀሳብ አለኝ፡፡

"እንደ ሀገር በርካታ ተግዳረቶች እያጋጠሙን ያሉት.. ታላቁ ቅዱስ መፅሐፍ ፧ስምቱን የሚገዛ ሰዉ ከተማን ከሚገዛ ይበልጣል፧የሚል ሀሳብ አለዉ ነገሮችን ከግዚአዊ ስሜታዊነት ነፃ ሆነን ብንመለከታቸዉ ለገጠሙን ችግሮች መፍትሄ የማግኘት እድላችን ሰፊ ነበር በይበልጥም ፖለቲከኞቻችንና ደጋፊዎቻቸዉ ከስሜታዊነት ነፃ ሆነዉ በምክንያታዊነት ላይ ተመስርተዉ ርዕዮተ-ዓለማቸዉን ብያራምዱ ሀገራችን በተሻለ ሁኔታ ላይ ትገኝ ነበር::"

ብዙዎች በስሜት..ሆ..ሆ.. ብለዉ እኩይ ተግባር ፈፅመዋል ወይም ተፈፅሞባቸዋል በተለይም በወጣትነታቸዉ የዕድሜ ክልል ዉስጥ የሚገኙ ዜጎች በሀገር ደረጃ ሁኔታዎች ሲከሰቱ ለመልካምም ሆነ ለመጥፎ ነገር ቶሎ ወደ ዉሳኔ ከመድረሳቸዉ በፊት ቆም ብሎ ማመዛዘን ይጠበቅባቸዋል፡፡

እንደ ማህበረሰብ እኛ ኢትዮጵያዉያን አብዛኞቻችን በሚባል ደረጃ ስሜቶቻችንን የመግራት ችግር ያለብን ይመስለኛል (በተለይም በፖለቲካዉ መስክ) ስሜታዊ ከመሆናችንም የተነሳ ይመስላል::

እንደ ሀገር በርካታ ተግዳረቶች እያጋጠሙን ያሉት.. ታላቁ ቅዱስ መፅሐፍ ፧ስምቱን የሚገዛ ሰዉ ከተማን ከሚገዛ ይበልጣል፧የሚል ሀሳብ አለዉ ነገሮችን ከግዚአዊ ስሜታዊነት ነፃ ሆነን ብንመለከታቸዉ ለገጠሙን ችግሮች መፍትሄ የማግኘት እድላችን ሰፊ ነበር በይበልጥም ፖለቲከኞቻችንና ደጋፊዎቻቸዉ ከስሜታዊነት ነፃ ሆነዉ በምክንያታዊነት ላይ ተመስርተዉ ርዕዮተ-ዓለማቸዉን ብያራምዱ ሀገራችን በተሻለ ሁኔታ ላይ ትገኝ ነበር::

ከዚህ ይልቅ ጭፍን በሆነ ስሜታዊነት ጥላቻን እየወለዱ ማህበረሰባችን እርስ በርስ ወደ አለመግባባት ደረጃ እንዲደርስ አድርገዉታል እኔና የእኔ ብቻ ትክክል ነዉ የሚል ግትር ስሜት የወለደዉ አቋም እንደ ግለሰብም ሆነ እደንደ ማህበረሰብ ከፍ ሲል እንደ ሁገርብዙ ርቀት ሊያስጉዘን አልቻለምም አይችልምም::

ይለቁንም በምክንያታዊነት በማመን ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን ብንፈጥር በህይወታችን እርካታን የምናገኝ ይሆናል፡፡

ሌላዉ የአብዛዉ ማህበረሰባችን ችግር ወረተኛ መሆን ይመስለኛል ወረተኛ የሆነ ሰዉ ቋሚ የሆነ አቋምና ዓላማ የለዉም ሁሉን ነገር የሚከዉነዉ በወረት ስለሆነ ዘላቂ የሆነ ዉጤት ያለዉ ፍሬ ነገር አይታይበትም ያዝ ለቀቅ አገም ጠቀም ዓይነት ሁኔታ በህይወቱ ይከሰታል ወረተኛ ሰዉ ስልቹ ነዉ ከብዙ ትግል በኂላ ለሚገኝ የህይወት ስኬት አይበቃም በሌሎች ዘንድ የመታመን ደረጃዉ ዝቅተኛ ነዉ እደነዚህ ያሉ ወገኖች ፍቅራቸዉም ይሁን ጥላቻቸዉ በወረት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ጊዚአዊ ነዉ፡፧

ወረተኝነት እንደ ማህበረሰብ ሲታይ በብዙ ጎኑ ጎጅነቱ ያመዝናል በወረት የተሰራ ሥራ ወረቱ ሲያልቅ አስታዋሽ ስለማይኖረዉ ዘላቂ በሆነ መልኩ ለሕዝብ ጥቅም ሊዉል አይችልም በወረት ዘመቻ ወጥተን የተከልነዉ ችግኝ በዘላቂነት እንክብካቤ ስለማይደረግለት አድጎ ለዛፍ አይደርስም ለዚሕም ይመስላል በእኛ ሀገር በየ አመቱ የአረንጓዴ ልማት እተባለ በዘመቻ መልክ በአንድ ሰሞን ሁላችንም ችግኝ ተካይ እንሆናለን ነገር ግን ከተከልን በኂላ በአብዛኛዉ እንክብካቤ ስለማናድረግ ፀድቆ አይገኝም በዚህም ካቻምና በተከልበት ሥፍራ ዘንድሮም ስንተክል እንታያለን::

ዓለም እያስጨነቀ ያለዉ የኮረና ቫይረስ ወደ ሀገራችን ገባ በተባለ ሰሞን የነበረን ስጋትና ጥንቃቄዎች ከሚገባዉ በላይ እደነበረ ሁላችንም የምናስታሰዉ ሀቅ ነበር ዛሬ ላይ ወረርሽኑ እየከፋ ቢመጣም የኛ ጥንቃቄ ወረቱ ስላለቀ ቸል በማለታችን ብዙ ወገኖቻችንን በበሽታዉ ሳቢያ እያጣን እንገኛለን ፡፡

ወረተኞች ሲበዙ በማህረሰብ ዉስጥ ጥርጣሬና አለመተማመን ይፈጠራል ለዚህም ይመስላል ፧አንቺ ወረተኛ ወረት የለመድሽዉ ሲያምንሽ እከዳሽ ልቤን አደማሽዉ፧ እያለ የድሮ ዘፋኝ ያዜመዉ እናም የዘመኔ ትዉልድ በስሜትና በወረት ባህሪ የተጠቃ ይመስለኛል እንደ ሀገር ያሉብንን ችግሮች ከስሜትም ከወረትም ነፃ ወጥተን ለመፍታት እንሞክር::

ትዉልዱ በምክናያታዊነት የሚያምን እድሆንና የሞራል ልዕልና እንድኖረዉ ቤተሰብ፧ መምህራና ሙህራኖቻችን ከፍተኛ የሆነ ሚናቸዉን በትጋት ሊወጡ ይገባል በይበልጥም አሁን ባለንበት ወቅት ሀገራችንን ከመፍረስ ለመታደግ እያንዳንዳችን በማስተወል ፅንፈኝነትን ወደ ጎን ትተን ከስሜታዊነት በፀዳ መልኩ የምናስበዉን በጎ ነገር እንከዉን ችግር ፈች በሆነ ሀሳብ ላይ እስከመጨረሻዉ በዓላማ እነትጋ ያኔ ከድል በኂላ የእርካታና ደስተኛ ህይወት ይኖረናል::

## ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኝነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርቡበታል

# ፋና ወጊ ተግባር በተማሪዎች

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የህብረተሰብ ጤና ት/ቤት የሚማሩ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ለአብነትና ለዓለማዊ ት/ቤቶች የመፀዳጃና ሌሎች አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች በመስራት አንገብጋቢ ተግዳሮቶችን መፍታታቸው ይፋ ሆነ

የኮሌጁ ማህበረሰብ አቀፍ ትምህርትና ማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ኡመር ሰይድ ልማታዊ የቡድን ስራው የማህበረሰብ ጤና ት/ቤት በመደበኛውና በተከታታይ መርሃ ግብር የሚማሩ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመተባበር ምንም ዓይነት በጀት ሳይመደብ የሚከናወን ስራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አክለውም በባህር ዳር ከተማ የሚታዩ ተግዳሮቶችን ለይቶ በማውጣት ሁሉን በአንድ ጊዜ ማድረስ ባይቻልም የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመምረጥ በተለያዩ የአብነትና የዓለማዊ ት/ቤቶች ላይ ተማሪዎች በፅንሰ ሃሳብ የተማሩትን ወደ ተግባር በመለወጥ መሬት የነካ ስራ መስራታቸውን አስገንዝበዋል፡፡




የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ለአብነት ተማሪዎች የሰሩት መኖሪያ ቤት ጉብኝት ሲደረግ

በጉብኝቱ የታዩት ግዮን አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ላይ ሴት ተማሪዎች የወር አበባ በሚያዩበት ወቅት የንፅህና መጠበቂያ ሞዴስ የሚቀይሩበትና የሚያርፉበት ክፍል እስከ ሞዴስ ማስቀመጫው ሽልፍ ድረስ ሰርተው ማስረከባቸው ት/ቤቱ ካለበት በርካታ ተግዳሮቶች መካከል አንዱና አንገብጋቢ የሆነውን መቀረፍ እንደቻሉ ርዕሰ መምህሩ አቶ ታገሰ ሌንጫሞ ከምስጋና ጋር ገልፀዋል፡፡

ፕሮጀክቴን የሰሩት ተማሪዎች ተወካይ አቶ ምንይችል ብርሃኑ 21 ተማሪዎች ተመድበው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመነጋገር የተሰራ እንደሆነህ አንድ ልጃገረድ ለመጀመሪያ ጊዜ የወር አበባ በምታይበት ወቅት የሚሰማትን ስሜት የሷን ማማነት በማይገልፅ መልኩ በኮድ እንድትፅፍና ለሌሎች ተሞክሮ እንዲሆን ለማድረግ አብረው እየሰሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ሌላው የጉብኝቱ አካል ምስራቀ ፀሐይ አዲሱ ሚካኤል የአብነት ት/ቤት ሲሆን ከ250 በላይ ተማሪዎች መኖራቸውንና ምንም አይነት መፀዳጃ ቤት ይቅርና ባዶ ሜዳ እንኳ ባለመኖሩ በግለሰቦች መኖሪያ ቤት አካባቢ ሲፀዳዱ ከፍተኛ ችግርና እንግልት ይደርስባቸው እንደነበር ችግሩ ተለይቶ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመተባበር መፀዳጃ ቤትና ልብስ የሚያጥቡበት ገንዳ እንዲሁም የእጅ መታጠቢያ ቧንቧ መሰራቱን የገለፁት የተማሪዎች ተወካይ አቶ አለማየሁ ደስታ ናቸው፡፡

የቤተክርስቲያኑ ዋና ፀሐፊ ቀሲስ ተመስገን በቀለ ቤተክርስቲያኑ የራሱ የሆነ የከርሰ ምድር ውሃ ስላለው ተማሪዎች የውሃ ችግር ባይገጥማቸውም መፀዳጃ ቤት ባለመኖሩ በግለሰቦች አትክልት ስፋራ ሲፀዳዱ ድብደባ ሁሉ ይደርስባቸው እንደነበር ገልፀው አሳሳቢና ወቅታዊ ለሆነው ችግር መፍትሄ መሰጠታቸው ይበል የሚያሰኝ አኩሪ ተግባር መሆኑን ከምስጋና ጋር ተናግረዋል፡፡

የጎብኝቱ መዳረሻና ዘርፈ ብዙ ተግባራት የተከናወነበት ጽርሓ አርያም ደብረሲና ባአታለማርያም ቤተክርስቲያን ላይ የሚገኘው የአብነት ት/ቤት የመኖሪያ ቤት እጥረት፣መፀዳጃ ቤት አለመኖርና የውሃ ችግር ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን ለይተው በአካባቢው ማህበረሰብ ድጋፍ መስራታቸውን የገለፁጽት ዶ/ር ደረጀ በዳኔ የህክምና ት/ቤት ም/ዲንና በመማር ላይ ስላሉ የቡድኑ አስተባባሪ ናቸው፡፡

አስተባባሪው አክለውም በቅድሚያ በመኖሪያ ቤቱ መተፋፈግ ምክንያት የተከሰተውን የ30 ተማሪዎች የሰውነት ማሳከክ በሽታ በዩኒቨርሲቲው ባለሙያች እንዲታከሙ ከማድረግ እንደጀመሩና መኗሪያ ቤት፣ሽንት ቤት የልብስ ማጠቢያ ገንዳ ጭምር እንዲሁም የውሃ ጉድጓድ በማስቆፈር የውሃ ችግሩንም መቅረፋቸውን አስገንዝበዋል፡፡

የቤተክርስቲያኗ ዋና ፀሐፊ ርዕሰ ደብር ናሁሰናይ እንግዳው ቅዱስ ያሬድ ትምህርትን እንዳስጀመረ ሁሉ እናንተም እኛ ጥሪ ሳናቀርብ በፈጣሪ ፈቃድ መጥጣችሁ ይህን የመሰለ ተግባር ማከናወናችሁ አድንቀው ለዩኒቨርሲቲው የምስክር ወረቀት አበርክተዋል፡፡

የጉብኝቱ ተሳታፊዎች የኮሌጁን ዋና ስራ አስፈፃሚ ፕ/ሮ የሽጌታ ገላውና የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዘዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈረውን ጨምሮ የዩኒቨርሲቲቀውና የኮሌጁ ከፍተኛ አመራሮች፣ ዲኖችና የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎች ይገኙበታል፡፡

ፕሮፌሰር የሽጌታ ገላው ይህ የልማታዊ የቡድን ስራ ፅንሰ ሃሳቡ የመነጨው ከጅማ ዩኒቨርሲቲ መሆኑን ገልፀው ፅንሰ ሃሳቡን ወደ ተግባር በመለወጥ በአጭር ጊዜ ሰፊ ስራ መስራት መቻሉ እጅግ በጣም አኩሪ ተግብር መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ፕሮፌሰሩ በማስከተል የአብነት ት/ቤት ለእሳቸውም አሁን ለደረሱበት ደረጃ ለመድረስ የመሰረት ድንጋይ የጣለና ታላቅ ትውስታን የጣለ መሆኑን አውስተው እነዚህ የማይታዩ ተቋማት ላይ መስራት ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንዳሉትና የሊቃውንት መፍለቂያ ለሆነው ተቋም ችግር መድረስ ይበል የሚያስብል ተግባር ነውና ለወደፊትም ከዚህ በተሻለ መልኩ መስራት የሚቻልበትን እንዲሁም የአብነት ተማሪዎች የጤና እክል በሚያጋጥማቸው ወቅት በነፃ የሚታከሙበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ተስፋየም በበኩላቸው ለታዩት ስራዎች ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱት አካላት ምስጋና አቅርበው የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ተልኮም አገር በቀል እውቀትን ወደ ምርምሩ በማምጣት ልማትን በተቀናጀ መልኩ መስራት ተገቢ እንደሆነ አስገንዝበው ይህም ተግባር አንዱ ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አቶ ኡመርም በማጠቃለያው ይህ የልማታዊ ቡድን ት/ት የተቀናጀ ስራን ስለሚሻ የወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት ወደተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ዩኒቨርሲቲው ድጋፍና ክትትል ማድረግ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

የአብነት ተማሪዎችም ለተደረገላቸው ነገር ሁሉ ደስተኛ መሆናቸውን በቅኔ ዘረፋ ምስጋና አቅርበው በአባቶች ፀሎት ተደርጓል፡፡

# ጤንነት

## የዩኒቨርሲታችን ምሁር በላቀ መምርምር ስራቸው የለም አቀፍ ሽልማት አገኙ



የ19ኛውን Tore Godal prize Award ተሸላሚዎች በማግኖሊያ ሆቴል፣ አዲስ አበባዶ/ር ሊያ ባለችበት ሽልማቱን ሲቀበሉ

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የሕክምና ላቦራቶሪ ሣይንስ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት አቶ ተዋቸው አወቀ የ19ኛው የቶሬ ጎዳል ሽልማት አሸናፊ ሆኑ::

ወጣቱ ተመራማሪ “Phenotypic and genotypic antimicrobial resistance profiles of Klebsiella pneumoniae isolated from patients at Tikur Anbessa Specialized Hospital, Addis Ababa, Ethiopia “ በተሰኘ የምርምር ስራቸው ለመሸለም በቅቷል።

የአርማወር ሀንሰን የምርምር ኢንስቲትዩት በተቋሙ የቀድሞ አመራር ቶሬ ጎዳል ስም በየዓመቱ ለወጣት ተመራማሪዎች የቶሬ ጎዳል ሽልማት ይሰጣል።

በመድረኩ የተገኙት የጤና ሚኒስትሯ ዶ/ር ሊያ ታደሰ ተመራማሪዎችን በማገዝ ችግር ፈቺ የሆኑ ምርምሮች ላይ ትኩረት መደረግ አለበት ብለዋል።

አሸናፊው የሜዳሊያ፣ ሰርተፊኬት እና የ15 ሺህ ብር ሽልማት ተበርክቶለታል።

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ላቦራቶሪ ሣይንስ ትምህረት ክፍልም አቶ ተዋቸው አወቀን እንኳን ደስ አለህ በማለት ወደፊትም ከዚህ የበለጠ እንደሚሰራ እምነት እንዳለው ገልጿል።

መግቢያ

ክለብሴላ ኒሞኔ (Klebsiella pneumoniae) የተባለዉ ባክቴየሪያ ከቀላል እስከ ሞት የሚደርስ በሽታ ያመጣል። ይህ ባክቴሪያ በአብዛኛዉ ተኝተዉ የሚታከሙ እና በእድሜ ገፋ ያሉ፤ ህፃናትን እንዲሁም ተጓዳኝ በሽታ ያለባቸዉን ያጠቃል። እነዚህ ሰዎች ላይ የደም ቧንቧ (Bloodstream)፤ የሽንት ቧንቧ (urinary tract)፤ ቁስል ላይ (Wound)፤ የሳንባ በሽታ (pulmonary infection) እንዲሁም ሌሎች በሽታዎችን የሚያመጣ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ለአብዛኛዉ መድሃኒቶች የተላመደ (Multidrug resistance) በመሆኑ ለህብረተሰብ ጤና አስጊ ሆኗል።

ብዙ መድሃኒቶች የተላመደ ክለብሴላ ኒሞኔ (Multidrug resistance K. pneumoniae) በብዙ የዓለማችን ክፍል የሚገኙ ሆስፒታሎች ላይ ወረርሽኝ ያስከተለ ሲሆን በኢትዮጵያ ግን ይህ ባክቴሪያ ምን ያክል መድሃኒቱን እንደተላመደ የሚያሳዩ ጥናቶች ዉስን ናቸዉ። ስለሆነም የጥናቱ አላማ በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከሚታከሙ ሰዎች ከተወሰደ ናሙና ላይ የተገኘ ክለብሴላ ኒሞኔ ባክቴሪያ የትኞችን መድሃኒቶች እንደተላመደ እና እንዲላመድ ያደረገዉን ዉስጣዊ ባህርይ (resistance encoding genes) ማወቅ ነዉ።ጥናቱ የተደረገዉ ከመስከረም እስከ ጥር 2011 ዓ.ም ሲሆን 132 ክለብሴላ ኒሞኔ ባክቴሪያ የተገኘባቸዉ ታካሚዋች ተሳታፊ ሆነዋል፡

የጥናቱ ጥቅሞች

1. ይህ ባክቴሪያ የትኞቹን መድሃኒቶች እንደተላመደ አዉቆ እነሱን ለታካሚዎች ላለመጠቀም (ያልተላመዳቸዉን ለመጠቀም) ይረዳል
2. መድሃኒትን ለመላመድ የሚያስችላቸዉ ዉስጣዊ ባህርይ (gene) ከአንዱ ባክቴሪያ ወደ ሌላ ባክቴሪያ እንዲሁም ባክቴሪያዎች ድግሞ ከአንድ ሰዉ ወደ ሌላ ሰዉ ስለሚተላለፉ ደረጃዉን አዉቆ ተገቢዉን ጥንቃቄ እና የመከላከል እረምጃ ለመዉሰድ ይረዳል።
3. እኛ ጋር ያለዉን የዚህን ባክቴሪያ መድሃኒት የመላመድ ደረጃ ከሌላው አለም ጋር ለማዎዳደር ይጠቀማል
4. ሰፋ ያለ ጥናት ለማጥናት እንደ ቅርብ መረጃ ያገለግላል

የጥናቱ ግኝቶች

በዚህ ጥናት ዉስጥ ከተካተቱት 132 ክለብሴላ ኒሞኔ ባክቴሪያዎች ዉስጥ 128ቱ (97%) Cefotaxime እና Ceftriaxone፤ 124 ቱ (93.9%) Trimethoprim-sulfamethoxazole እንዲሁም 111 (84.1%) Cefepime የሚባሉ መድሃኒቶችን የተላመዱ ሁነዉ ተገኝተዋል። ሁለት ክለብሴላ ኒሞኔ ባክቴሪያዎች በዚህ ጥናት ለተካተቱት 21 መደሃኒቶች ለሁሉም የተላመዱ ሁነዋል። በአንፃራዊነት ከ 132 ክለብሴላ ኒሞኔ ባክቴሪያዎች ዉስጥ 123 ቱ (93.2%) ለ Amikacin 107፤ (81.1%) ለ Imipenem እና 96 (72.7%) ለ Meropenem ያልተላመዱ ሆነዉ ተገኝተዋል። በዚህ ጥናት መድሁኒቶችን እንዲላመዱ የሚያደርጋቸዉ ዉስጣዊ ባህሪዎችም (resistance encoding genes) ከፍ ያሉ ሆነዉ ተገኝተዋል። ስለሆነም መድሃኒትን በአግባቡ የመጠቀም ባህልን ማጎልበት፤ ባክቴሪያዎች መድሃኒትን የመላመድ ደረጃቸዉን መከታተል እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ሰፋ ያሉ ጥናቶች ቢደረጉ መልካም ነዉ አላለሁ።

ተዋቸዉ አወቀ
ህክምና ላብራቶሪ ሳይንስ ትምህርት ክፍል፣ ህክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ


**እንኳን ደስ አለህ!!!!**

Nile 7th year; publication No.8; June, 2021

# ኪነጥበብ እና ባህል

## ስለ“አያሌው ሞኙ”በጥቂቱ…( ከfacebook ገፅ የተወሰደ)

በተለያዩ የባህል ዘፈኖች “አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ፣ ሠው አማኙ” ሲባል ሰምተናል። እኔ በበኩሌ እኚህ አያሌው የሚባሉት ሠው የምናብ ወይም የተረት ፈጠራ ሠው ይመስሉኝ ነበር። ይሁንና ሰሞኑን ያነበብኩት መጽሐፍ (“የ21ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጲያ አንደኛ መጽሐፍ ፲፱፻ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም” በጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ- የመጀመሪያ ዕትም ፲፱፻፺፮ ዓ.ም) አያሌው በህይወት የነበሩ ግለሰብ እንደነበሩ ያስረዳል:::: ስለሳቸው ከመጽሐፉ ከተጠቀሰው በጥቂቱ እነሆ፦




“በወቅቱ የጥብቅና ትምሕርት የነበረው የኢጣልያ ቆንሲል ራፋኤል ዲ ላውሮ የሚባል ጎንደር ውስጥ ተቀማጭ ሆኖ ራስ ጉግሣን ወዳጅ ለማድረግ መሬት ተከራይቷቸው እያለ የተፈሪን ወደ አውሮፓ ሥልጣኔ ማዘንበል እያጥላላ ያጫውታቸው ነበር፡ በመሃሉ የራስ ጉግሣን አጎት ደጃች አያሌውን ንጉሥ ተፈሪ በሹመት በማባበል ራስ ጉግሣን አብረዋቸው እንዲወጉና ጎንደርንም ከግዛታቸው ጋር እንዲደርቡ ቃል ገብተው አሳመኗቸው። ራስ ጉግሣን ወደ አዲስ አበባ ሲጠሩ አልመጣም በማለታቸው ራስ ሙሉጌታ ጦር ይዘው ሊወጉዋቸው ሄዱ። ንጉሥ ተፈሪ የጎንደርን ሕዝብ ራስ ጉግሣን ከረዳህ ከመሬትህ ትነቀላለህ ብለው ስላወጁ ጦርነቱ ሲጀመር ራስ ጉግሣ ብቻቸውን ቀሩና ተገደሉ። ደጃች አያሌውም ከራስ ጉግሣ ሞት በኋላ እሾማለሁ ብለው ሲጠብቁ ሌላ ሰው ተሾሞ መሳቂያ ሆኑ። የጎንደር ሰውም

“አያሌው ሞኙ፤

ሰው አማኙ፤ሰው አምኙ”

ብሎ ዘፈነባቸው።

በዚህ ጦርነት የደቡብ ጎንደር ሕዝብ ራስ ጉግሣን ባለመርዳቱ እያዘነና ሲሞቱ ረግመውናል በማለት እስከ



አያሌው ሞኙ ፊታውራሪ አያሌው ብሩ ናቸው።ፊታውራሪ አያሌው ብሩ የራስ ብሩ ወልደሚካኤል ልጅ እና የእትጌ ጣይቱ የቅርብ ዘመድ ናቸው።

ፊታውራሪ አያሌው የወገራ አውራጃ ሹመኛ፣ የጎንደር አስተዳዳሪ እና በአፄ ሀይለስላሴ ዘመን የንጉሰ ነገስቱ ጦር አዛዥ ነበሩ። ፊታውራሪ በመኢሶ ጦርነት ልጅ እያሱ እንዲወድቅ ፣በአንቺም ጦርነት ራስ ጉግሳ ስልጣን እንዲለቅ በማድረግ አፄ ሀይለስላሴ ስልጣን እንዲይዙ አድርገዋል።

አፄው ለዚህ ሁሉ ውለታው የራስነት ማዕረግ እንደሚሰጧቸው ለአያሌው ሞኙ ቃል ገብተውላቸው ነበር።

ዳሩ ግን አፄ ሀይለስላሴ የስልጣን መንበራቸውን ካስተካከሉ በኋላ አያሌው ብሩን ፊት ነሷቸው። ምክንያቱም፣ ፊታውራሪ አያሌው ፣የእትጌ ጣይቱ የቅርብ ዘመድና የአፄ ሚኒሊክ ባለስልጣናት የቅርብ ወዳጅ ስለነበሩ ወንበሬን ሊጋፉ፣አመፅም ሊያስነሳብኝ ይችላል በማለት ለፊታውራሪ አያሌው የተሻለ ማዕረግ ሳይሰጧቸው ቀሩ።

እንዳውም ከንጉሡ የክብር ፕሮቶኮልነት ሁሉ አውርደው በቅጣት ወደ አርሲ ላኳቸው። አያሌውም የገዛ ዘመዶቻቸውን ተዋግተው ስልጣን አሳልፈው ለአፄ ሀይለ ስላሴ መስጠታቸውን እንደ ረመጬት ፈጃቸው።

አቃጠላቸው።ይሄን የተመለከቱ ደግሞ “ አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ “አያሌው ሞኙ ንጉስ አማኙ” እያሉ ዘፈኑባቸው። ዘፈኑም ባህል ሁኖ እስከዛሬ ድረስ በጎንደር ፣በጎጃም፣በወሎ በስፋት ይዜማል።

_ የሸህሳብ አበራ - Ethiopian patriot in 20th century እና የ ከዲያቆን ዳንኤልን ክብረት “የተደበቀው ማስታወሻ” ጠቅሶ ለአማራ መገናኛ ኮርፖሬሽን እንደፃፈው_

## ችግር ፈቺ የምርምር ውጤት ከገፅ 4 የቀጠለ



በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ የእንቦጭ አረምን ለማስወገድ በሐይቁ ዳርቻ የተተከሉ የደንገል ተክል እና የእሳር ተክሎች በዩኒቨርሲቲው አመራሮች ሲጎበኙ

ሽፈራው ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት የምርምር ስራቸውን አቅርበዋል፡፡

በቦታው ተገኝተው የተማሪዎችን የመመረቂያ ፕሮጀክት የሆነውን የምርምር ስራ የተመለከቱት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው እንዳሉት ለወንዞቻችና

ለሀይቆቻቻችን ጠንቅ የሆነውን የእንቦጭ አረም ወደሚጠቅም ነገር መቀየራቸው ሐገሪቱ ለማዳበሪያ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ከማስቀረቱም በተጨማሪ የእንቦጭን አረም ለማስወገድ የሚደረገውንም የስራ ሂደት ስለሚያግዝ ጥራቱ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ናግረዋል፡፡

በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ በቡልቃ አበባ ጎጥ ነዋሪ የሆኑት እና የፈጠራው ተጠቃሚ የሆኑት አርሷደር የሺዋስ ጌናው እንዳሉት ተማሪዎች ለጣና ውሃ ስጋት የሆነውን የእምቦጭ አረም ተጠቅመው ያዘጋጁት ማዳበሪያ በማሳቸው የበቀለውን የቲማቲም ተክል በሚገባ በቅሎ ጥሩ ምርት ማግኘታቸው ተከትሎ በአካባቢው የሚኖሩ አርሳደሮች ማዳበሪያውን ለመጠቀም ከፍተኛ ተነሳሽነት ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ ነዋሪና አርሷደር የሆኑት አቶ መኬ አዱኛ የቲማቲም ተክል ሰርቶ ማሳያውን ከጎበኙ በኋላ በተማሪዎች የተዘጋጀውን ቨርሚ ኮምፖስት/የተፈጥሮ ማዳበሪያ

በመጠቀም የሚያመርቱትን ምርት ማሳደግ እንደሚፈልጉ ተናግረዋል፡ በቨርሚ ኮምፖስት የተፈጥሮ ማዳበሪያን ተጠቅመው በቲማቲም ተክል የተሸፈነውን የአርሷደሩ ማሳ እና የተመረተውን ምርት የቀበሌው ሊቀመንበርና የግብርና ባለሙያዎች እንዲሁም የአካባቢው አርሷደሮች ጎብኝተውታል፡፡

በተጨማሪም በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ የተከሰተውን የእንቦጭ አረምን ለማስወገድ የተፈጥሮ ሐብት ስራዎችን እየሰሩ ያሉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪ ዶ/ር ንብረት አስራደ በሐይቁ ዳርቻ የተከሏቸውን የደንገል ተክልን እና የአፈር መከላትን የሚከላከሉ እንዲሁም ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግሉ የእሳር ተክሎች አድገው ጥሩ ደረጃ ላይ በመሆናቸው በዶ/ር ተስፋዬ እና በሌሎች ከፍተኛ አመራሮች

## ‘ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት… ከገፅ 15

ዶ/ር ተስፋዬ፡- የጸጥታው ሁኔታ ኮቪድ-19 ተጨምሮበት ችግሩን እኛ ልናስወግደው የምንችል ስላልነበር ለዚያ የሚያስፈልገውን መፍትሄዎችን ጎን ለጎን ስንሰራ ነበር፡፡ ለምሳሌ መተካት የሚችለውን አካባቢ በቅርቡ እንዲሰሩ የማድረግ፣ ማህበረሰቡ ጋር የሚያገናኝ ከሆነ ደግሞ የኮቪድ ግንዛቤ በመፍጠር ድሮ በብዛት ስናሰለጥናቸው የነበረውን ቁጥራቸውን በመቀነስ በተለያየ ዙር በማድረግ በተጨማሪም ቨርችዋል ሲስተምን በመጠቀምና ማቴሪያሎች እንዲደርሷቸው በማድረግ ስልጠናዎችን እንሰጣለን፡፡ በተለይ ከውጭ የሚመጡ ፕሮጀክቶች ላይ እንደ ድሮው ገበሬዎችን ሰብስበን ማሰልጠን ላይ ከፍተኛ ማነቆ ነበር ነገር ግን ተወካዮችን በትንሽ ቁጥር አሰልጥነን እነሱ ደግሞ ሂደው ሲያሰለጥኑ ቨርችዋል ድጋፍ በማድረግ የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ነበሩ፡፡

ከግዥው ሂደት ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በተለይም ከውጭ ለሚደገፉ ፕሮጀክቶች ግብዓቶችን ባለቤቶች ከውጭ እንዲልኩ እናደርጋለን፡፡ ጨረታ ወጥቶ የሚያቀርቡ ድርጅቶችን የግዥ ሰራተኞችን ከአዲስ አበባ በቀጥታ እንዲገዙ በማድረግ የምንሰራበት ጊዜም አለ፡፡

ናይል፡- የቀጣይ አመት የትኩረት አቅጣጫዎችን ቢገልጹልን

ዶ/ር ተስፋዬ፡-የምርምር ዩኒቨርሲቲ ከመሆናችን ጋር ተያይዞ ምንም የተለየ አቅጣጫ ባንከተልም ከ10 አመት ስትራቴጂክ እቅዱ የተቀዳ እንደ ምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆን ያለብን የተቀመጡ አሉ የሰው ሀብት ልማትና የድህረ-ምረቃ ስራዎችን ከምርምሩ ጋር እንዴት አድርገን እናገናኝ የሚለውን ትልቅ ትኩረት አድርገን እንሰራለን፡፡

የፖስት ዶክ ፕሮግራምን በተመለከተ ከዚህ በፊት ዶክመንት አዘጋጅተን ያልሰራነው ምርምር ላይ ትልቅ አቅም ስለሚሆነን የፖስት ዶክ ፕሮግራም እንከፍታለን፡፡ የምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎቻችን አሁን ውጤት እንዲያመጡ ማድረግ አለብን፡፡ ካሁን በኋላ የተበጣጠሱ ስራዎችን አንሰራም ትኩረት አድርገን ለውጥ የምናመጣባቸውን የትኩረት አቅጣጫ ብለን ያስቀመጣቸው ላይ ትኩረት አድርገን በጀት እንመድባለን ስለዚህ ሁሉንም ማድረስ ሳይሆን በተወሰኑት ስራዎች ላይ አድምተን ለመስራት አቅደናል፡፡

የመምህራንን የምርምር ውጤት ወደ ማህበረሰቡ እንዲወርዱ አጠናክረን እንሰራለን፡፡ የግዥና የፋይናንስ ስርዓቱን ሊያግዝ የሚችል ራሱን የቻለ ሲስተም በመንግስትም የተፈቀደ አደረጃጀት በመሆኑ መምህራን አሁን የሚያሰሙትን እሮሮ ለመቀነስ በትኩረት እንሰራለን፡፡

ዋናው የትኩረት አቅጣጫችን ጣና ሀይቅና የህዳሴው ግድብ በመሆኑ ትልቅ ግምት ሰጥተን እንሰራለን፡፡ ህዳሴ ግድቡ ስንል ሁሉን ያማከለ ነው በፖለቲካው በውሃው በተፈጥሮ ሀብቱ በአጠቃላይ የማይመለከተው ሙያ ስለሌለ መምህራን ወደ ቦታው ሔደው ምርምሮችን እንዲሰሩ እንሰራለን፡፡

ናይል፡- በአጠቃላይ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎትን በተመለከተ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ

ዶ/ር ተስፋዬ፡- ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ትርፍ ስራ አይደለም የቅንጦት ስራም አይደለም መስራት ያለብን ግዴታችን መሆኑን ማህበረሰባችን እንዲገነዘብ እፈልጋለሁ፡፡ አንዳንዴ መምህራን እኛ የተቀጠርነው ለማስተማር ነው ብለው ይሞግታሉ በመንግስትም የተቀመጠውአቅጣጫ አንድ መምህር 60% ጊዜውን ለማስተማር 25% ጊዜውን የሚመራመርበት 15% ጊዜውን የማ/ሰብ አገልግሎት ሊሰጥበት ይችላል፡፡ መምህራን ይህንን አውቀው ለምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሁም ለቴክኖሎጂ ሽግግር እውቅና ሰጥተው ጊዜያቸውን ከፋፍለው እንዲሰሩ እንፈልጋለን፡፡ የምርምር ዩኒቨርሲቲ የመሆን እድሉ ሲሰጠን ከዚህ በፊት ከነበረው በተሻለ በአለም ዐቀፉ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውና የማ/ሰቡን ችግር መፍታት የሚችሉ ምርምሮችን መስራት ይጠበቅብናል

የድህረ ምረቃ ተማሪዎቻችን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንደመሆናቸው ከመምህራን ጋር ተባብረው በሚያገኙት አጋጣሚ በምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግርና በማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሳተፉ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ የአስተዳደርና የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞቻችንም ልክ እንደ መማር ማስተማሩ ለማ/ሰብ አገልግሎት ትኩረት በመስጠት ለዩኒቨርሲቲው ራዕይና ተልዕኮ መሳካት በቅንነት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ናይል፡- ስለቃለ-ምልልሱ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን፡፡

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# የተማሪዎች ተግባራዊ ችግር ፈች የምርምር ውጤት

በሙሉጌታ ዘለቀ




ተማሪዎች የጥናት ውጤታቸውን ለዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ አመራሮች ሲያስጎበኙ

**ከእንቦጭ አረም የተዘጋጀው ቨርሚ ኮምፖስት/የተፈጥሮ ማዳበሪያ ውጤታማ መሆኑ ተገለፀ**

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በጣና ሐይቅ ላይ የተከሰተውን እንቦጭ አረምን ለማጥፋት በተለያዩ ጊዜያቶች በርካታ ሙከራዎችን እና ድጋፎችን ሲያደርግ መቆየቱ ይታወሳል; በአሁኑ ሰዓት አረሙ በብዛት በተከሰተበት በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ በቡልቃ አበባ አካባቢ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በስነምድር ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ድግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ተማሪ ታድሎ በላይና ተማሪ ዳኛቸው አየነው የመመረቂያ ፕሮጅክታቸውን የእንቦጭን ብስባሽ፣ የእንቦጭን ቅጠል፣ የእንቦጭን ቅጠልና ግንዱን እንዲሁም የእንቦጩን ስር በማድቀቅ እና በወንፊት በመንፋት እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውስጥ እንቦጩን ወደ አፈርነት ለመቀየት ያስትል ዘንድ ትሎችን ተጠቅመው አራት አይነት ጠጣር ቨርሚ ኮምፖስት/የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲሁም በፈሳሽ መልክ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በማዘጋጀት በአርሷ ደሮች ማሳ ላይ የቲማቲም ተክል ሰርቶ ማሳያ ሲያደርጉ ቆይተው በ20/10/2013 ዓ.ም የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገለልግሎት ም/ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት የምርምር ስራቸውን አቅርበዋል፡፡

በቦታው ተገኝተው የተማሪዎችን የመመረቂያ ፕሮጀክት የሆነውን የምርምር ስራ የተመለከቱት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው እንዳሉት ለወንዞቻችና ለሀይቆቸቻችን ጠንቅ የሆነውን የእንቦጭ አረም ወደሚጠቅም ነገር መቀየራቸው ሐገሪቱ ለማዳበሪያ የምታወጣውን የውጭ ምንዛሬ ከማስቀረቱም በተጨማሪ የእንቦጭን አረም ለማስወገድ የሚደረገውንም የስራ ሂደት ስለሚያግዝ ጥራቱ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ በቡልቃ አበባ ጎጥ ነዋሪ የሆኑት እና የፈጠራው ተጠቃሚ የሆኑት አርሷደር የሺዋስ ጤናው እንዳሉት ተማሪዎች ለጣና ውሃ ሰጋት የሆነውን የእምቦጭ አረም ተጠቅመው ያዘጋጁት ማዳበሪያ በማሳቸው የበቀለውን የቲማቲም ተክል በሚገባ በቅሎ ጥሩ ምርት ማግኘታቸው ተከትሎ በአካባቢው የሚኖሩ አርሳደሮች ማዳበሪያውን ለመጠቀም ከፍተኛ ተነሳሽነት ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ ነዋሪና አርሷደር የሆኑት አቶ መኬ አዱኛ የቲማቲም ተክል ሰርቶ ማሳያውን ከጎበኙ በኋላ በተማሪዎች የተዘጋጀውን ቨርሚ ኮምፖስት/የተፈጥሮ ማዳበሪያ በመጠቀም የሚያመርቱትን ምርት ማሳደግ እንደሚፈልጉ ተናግረዋል፡፡

በቨርሚ ኮምፖስት/የተፈጥሮ ማዳበሪያን ተጠቅመው በቲማቲም ተክል የተሸፈነውን የአርሷደሩ ማሳ እና የተመረተውን ምርት የቀበሌው ሊቀመንበርና የግብርና ባለሙያዎች እንዲሁም የአካባቢው አርሷደሮች ጎብኝተውታል፡፡

በተጨማሪም በሽሀ ጎመንጌ ቀበሌ የተከሰተውን የእንቦጭ አረምን ለማስወገድ የተፈጥሮ ሐብት ስራዎችን እየሰሩ ያሉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህር እና ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ንብረት አስራደ በሐይቁ ዳርቻ የተከሏቸውን የደንገል ተክልን እና የአፈር መከላትን የሚከላከሉ እንዲሁም ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግሉ የእሳር ተክሎች አድገው ጥሩ ደረጃ ላይ በመሆናቸው በዶ/ር ተስፋዬ እና በሌሎች ከፍተኛ አመራሮች ተጎብኝቷል፡፡



በምርምር ውጤቱ ተጠቃሚ የሆነ አርሶ አደር በቲማቲም ማሳው

ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# መሪነት እና የኃይል አጠቃቀም

*አይንእንግዳ አዳሙ*
*በጤና ሥርዓት ሥራ አመራር እና ምጣኔ ሀብት ረዳት ፕሮፌሰር*

## እንደ መግቢያ

በመሪነት ጥናት ልዩ ትኩረት ከሚያገኙ እና ብዙ ትንታኔዎች ከሚቀርብባቸው አበይት ጭብጦች {አርእስተ) ጉዳዮች አንዱ የኃይል ጉዳይ ነው። ኃይል (Power) አንድ መሪ የመሪነት ሥራውን በሚገባ እንዲያከናውን ከሚያስፈልጉት ግብዓቶች አንዱ ነው። ኃይል ማለት መሪው የተከታዮቹን{የተመሪዎቹን} ጸባይ ለመቆጣጠር እና የነገሮችን አቅጣጫ ለመወሰን ለመሪው የሚያስፈልገው አቅም ማለት ነው:: በሌላ አባባል ሰዎች እንዲሁ ሊሠሩት የማይችሉትን ነገር ለማሰራት የሚያግዝ የመሪው መሰሪያ ነው።

ኃይልን መጠቀም ማለትም መሪውተከታዮቹ እና የውሳኔ ሐሳቦች ላይ ተጽእኖ በማሳደር ሥራዎችን ማሠራት ወይም አለማሠራት ማለት ነው።በአጠዋላይ መሪነት ማለት ትርጉሙ ተጽእኖ የማሳደር ሄደት ነው ተብሎ ይተረጎማል::

ኃይል ጠቃሚ እንዲሆን መሪው ሊጠቀምበት ይገባል። ስለዚህ ተጽእኖ ማሳደር (ማሳረፍ ) የመሪነት አስኳል (ልብ) ነው። በስፋት የሚታወቁ ልዩ ልዩ የኃይል አይነቶችን እና ምንጮቻቸውን ከዚህ ቀጥለን አጠር ባለ መልኩ እንመለከታለን።

## የኃይል አይነቶችና ምንጮቻቸው

አንድ መሪ ኃይል ያስፈልገዋልካልን ምን አይነት ኃይል ነው የሚያስፈልገው? ይህን ኃይል የሚያገኘው ስከየትነው? የሚሉ ጥያቄዎች መሠረታዊ ናቸው።

ብዙ የኃይል አይነቶች ቢኖሩም ዋና ዋና የሚባሉትን ከዚህ ቀጥሎ እናያለን። ጠቅለል ባለ መልኩ መገኛ ምንጫቸውን ስናይ ግን ከሥልጣን የሚገኙ እና ከመሪው ከራሱ (ከእውቀት፣ ልምድ፣ ክህሎት እና ሰብአዊ ጠባይ) የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ሀ.ቅቡልሥልጣናዊኃይል(Legitimate Power):** ይህ ኃይል አንድ መሪ የመሪነት ሥልጣንን በሹመትም ይሁን በምርጫ ሲሰጠው አብሮ የሚሰጠው ቅቡልነት ያለው ኃይል(Legitmate Power) ነው። ይህም ማለት መሪው ሥልጣን ሲሰጠው ሁለት የማይነጣጠሉ ነገሮች ማለት ኃላፊነትና ሥልጣን (Responsibility and Authority) በአንድ ላይ ነው የሚሰጡት። ይህ ሥልጣን ማለት ደግሞ ለተሰጠው የሥልጣን እርከን ይመጥናሉ የተባሉ ነገሮች ላይ የመወሰን ሥልጣኑን ተጠቅሞ ሥራዎችን የማሠራት፣ የነገሮችን አካሄድ እርሱ በፈለገው መንገድ እንዲሄዱ የማስቻል አቅም ይሰጠዋል ማለት ነው። ስለዚህ የዚህ ኃይል ምንጩ ሥልጣን ነው ማለት ነው። ይህን ነው ቅቡል ሥልጣናዊ ኃይል የምንለው።

**ለ.የመሸለም ኃይል (Reward Power) እና የመቅጣት ኃይል (The Power to Punish)**


እነዚህ ሁለት የኃይል አይነቶች ከቅቡል ሥልጣናዊ ኃይል ጋር አብረው የሚሰጡ ኃይሎች ናቸው። ይህም ማለት መሪው በጎለሠራው ተከታዩ ሊሸልመው፡ ሰነፍ፣ አጭበርባሪ እና ሥራ የማይወድን ተከታዩን ደግሞ ሊቀጣ የሚችልበት ኃይል አለው ማለት ነው። መሪው የመሸለም እና የመቅጣት ኃይሉን ተጠቅሞ ሥራዎችን ማሠራት ይችላል።

የመሪነት እና ኃይል ግንኙነት ሲተነተን ከሚጠኑ ነገሮች አንዱ የኃይል ርቀት/ልዩነት (power distance) ነው። በተቋማት ውስጥ ያለው ያልተመጣጠነ የኃይል ስርጭት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለው የቅቡልነት ደረጃ የኃይል ርቀት ይባላል። ይህ የኃይል ርቀት/ልዩነት ከፍተኛ በሆነበት ማኅበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት የመሸለም እና የመቅጣት ኃይል ትልቅ ሚና አላቸው።

ለምን ቢባል መሪው የያዘዘውን እና የወሰነውን ውሳኔ ትክክል ባይሆን እንኳን ለምን ብሎ የመሞገት እና ተቃራኒ ሀሳብ የማንጸባረቅ ባህሉ ስለሌለ ሁሌም መሪው ተፈርቶና ተከብሮ ትእዛዞቹም ተፈጻሚ ስለሚሆኑ ነው።

እነዚህ ከላይ ያየናቸው የኃይል አይነቶች ከሥልጣን(Authority) የሚመነጩ ሲሆኑ ሌሎች ከግለሰቡ ወይም ከመሪው የሚመነጩ የኃይል አይነቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው:: በእርግጥ አንዳንዶቹ ከሁለቱም ምንጮች ሊገኙ ይችላሉ።

**ሐ. ምሁራዊ ኃይል(Expertise Power):** አንድ ሰው፤ በተለይ መሪ የሚሆን ሰው ቢያንስ በአንድ የተወሰነ የሙያ ዘርፍ የተሻለ እና ተቀባይነት ያለው የተፈተነ እና የነጠረ እውቀት፣ ክህሎት እና ልምድ ሊኖረው ይገባል:: ይህም ማለት በዚያ የሙያ ዘርፍ ላይ ሰው ሲያስፈልግ ቀድመው ወደ ሃሳባችን እና አእምሯችን ከሚመጡት ምሁራን




ተርታ የሚያሰልፍ የእውቀት፣ ልምድ እና ክህሎት ደረጃ የደረሰ የትምህርትና የሙያ ዝግጅት ያስፈልገዋል ማለት ነው።

ይህ ሲሆን ሁሌም ለውሳኔ የሚፈለግ ተጽእኖ ፈጣሪ መሪ እንዲሆን ያስችለዋል። ይህም በትምህርት ዝግጅት እና በግልጥረት የሚገኝ እንጅ ሥልጣን ሲይዝ የሚታደለው አይደለም።

ሆኖም አንድ ሰው በመሪነት ቆይታው ብዙ ነገሮች ላይ ለመሳተፍ እድሉ እና መረጃው ስለሚኖረው ከተከታዮቹ የተሻለ ይህን ኃይል ገንዘብ የማድረግ እድል አለው። በተለይ ለመሪነት የሚያስፈልጉ የእውቀትና ክህሎት ዘርፎችን የመለማመድና የመቅሰም እንዲሁም የመተግበርና ማስተግበር እድል ስላለው ሙሉ በሙሉ የዚህ ኃይል አይነት ምንጩ የግል ጥረትና ግለሰባዊ ነው ለማለት አያስደፍርም።

ነገር ግን የመሪነት ወንበር ላይ ያልተቀመጡ እና ልዩ ልዩ ተጽእኖ ፈጣሪ የእውቀት ሰዎች ስላሉ እና ይህ ምሁራዊማንነታቸው ተጽእኖ ለመፍጠር ስለሚያስችላቸው ምሁራዊ ኃይል ከሥልጣን ውጭም ሊገኝ እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል።

**መ . የ ተ ጠ ቃ ሽ ነ ት ኃይል(Referent Power):** ይህ ደግሞ አንድ ሰው በበጎ ሥራው፣ በመልካም ፀባዩ፣ በታማኝነቱ፣ በእውነተኛነቱ በአጠቃላይ በመልካም ምግባሩና ግለሰባዊ ማንነቱ ተጠቃሽና ተጽዕኖፈጣሪ ሲሆን የሚላበሰው ኃይል ነው። ልክ እንደ ምሁራዊ ኃይል ሁሉ የተጠቃሽነት ኃይልም በዋናነት ከግለሰብ የሚመነጭ ሲሆን በሥልጣን ሊታገዝ ይችላል። እንዴት ቢባል ይህ የኃይል አይነት በአብዛኛው ለህግ በመታዘዝ፣ መመሪያን በማክበርና የሥነ-ምግባር መርሆዎችን በመፈጸም የሚገኝ ስለሆነ፡ መሪዎች ከተመሪዎች የተሻለ እነዚህን ህጎች፣ መመሪያዎችና መርሆዎች የማወቅ የተሻለ እድል ስላላቸውና ይህም ዕድል በሥልጣናቸው ምክንያት የተገኘ ስለሆነ ነው።

**ሠ. የመረጃ እና የማስረጃ ኃይል (Information Power)፡** ይህ የኃይል አይነት አንድመሪ ወይም ግለሰብ በተወሰነ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ ባለው መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚገኝ ኃይል ነው። ይህም በርዕሰ-ጉዳዩ ላይ ባለን የመረጃ ጥርቅምና ጥንቅር ላይ ይመሠረታል ለማለት ነው እንጅ ልክ እንደ ምሁራዊ ኃይል በጉዳዩ ላይ ባለው የተፈተነ፡ የነጠረ እውቀት፣ ልምድ እና ክህሎት የሚለካ አይደለም። መረጃ ኃይል ነው። በተለይ ውሳኔዎቹን እና ሥራዎቹን ሁሉ በመረጃ ላይ ተመሥርቶ በሚከውን ማኅበረሰብ ውስጥ መረጃ ትልቅ ኃይል ነው። መረጃ ካለህ ኃይል

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

## “ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ትርፍ ስራ አይደለም የቅንጦት ስራም አይደለም”

ሙሉጌታ ዘለቀ



ዶ/ር ተስፋዬ፡- ዶ/ርተስፋዬ ሽፈራው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት

ናይል፡- በቅድሚያ ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆንዎ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እያመሰገንን ሙሉ ስምዎትንናየስራኃላፊነዎትን ቢያስተዋውቁን?

ዶ/ር ተስፋዬ፡- ዶ/ርተስፋዬ ሽፈራው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት

ናይል፡- በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት በ2013 ዓ.ም እንደ ስኬት የሚቆጠሩ ስራዎችን ቢጠቅሱልኝ?

ዶ/ር ተስፋዬ፡- እሽ አመሰግናለሁ በ2013 ዓ.ም በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ትኩረት ሰጥተን ሥንሰራ የነበረው በአብዛኛው ወቅታዊ በሆኑ ጉዳዮች ማለትም ከኮቪድ-19 ወረሽኝ እና ጣና ላይ ያተኮሩ ሥራዎች፣ ከግብርና ዘርፎች ጋር ተያይዞ ካሁን በፊት የጀመርነው በሁሉም የዩኒቨርሲቲው ኮሌጅና ፋኩሊቲዎች የሜጋ ፕሮጀክት እየሰራን ነው::

ከኮቪድ ባሻጋር ቅድሚያ የሚጣቸውን ጉዳዩች ማለትም በአካባቢ ጥበቃ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ እንዲሁም በእንቦጭ አረም ሀገራዊ የንቅናቄ ዘመቻ ሥራ ትልቅ ባለድርሻ አካል ሁነን ሰርተናል።

ከአርንጓዴ አሻራ ልማት ጋር ተያይዞ በብር አዳማ አምስት የችግኝ ባቢያዎች እና በባሕር ዳር ከተማ ከኢኮ ቱሪዝም ጋር የምንሰራው የቤዛዊት ሳይትን በመጠቀም ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ችግኝ ተክለን ነበር።

ለ2013/14 በዚህ ዓመት ሐምሌ 15/2013 ዓ.ም የአገር በቀል ዕጽዋቶች ለመትከል ቅድመ ዝግጅት እያደረግን ነው።

በተጨማሪም ከዚህ አካባቢ ያለውን ልማት የሚያግዙ በየኮሌጆች እና ፋኩሊቲዎች ያሉ ፕሮጀክቶች በመጠቀም ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ የሚችል ከተፈጥሮ ሀብት ከአፈርና ውሃ ሀብት ጥበቃ ጋር ተያይዞ በርካታ ሥራዎችን ሰርተናል በተለይ ሜጫ አካባቢ በጣም የተጎዱ ቦታዎችን ህብረተሰቡን አስተባብረን በመስራታችን ረጅም እድሜ የሚቆዩ ዛፎች እና የፍራፍሬ ተክሎች በተለይ ደግሞ የአቦካዶ ተክሎች ተክለን ጥሩ ውጤት አምጥተናል።

ቆጋ አካባቢ የጠብታ መስኖ/drop irrigation ቴክኖሎጅም ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ርቀት ሄደናል።

በቴክኖሎጂ ሽግግርም በርካታ ቴክኖሎጅዎችን ከከሰል ማክሰያ ቴክኖሎጂ ጀምረን የፀሀይ ብርሃንን በመሰብሰብ ከኤሌክትሪክ መስመር ውጭ የሆኑ አካባቢዎችን የሶላር ተጠቃሚ አድርገናል በተለይ ደግሞ የጣና ገዳማት ላይ ትልቅ ሥራ ሰርተናል።

በተለይ ቆለላ አንድነት ትምህርት ቤት ሶላር በመግጠም ዲጂታላይዝድ በሆነ መንገድ ዘመናዊ የቤተ-ሙከራ እና የቤተ-መጽሐፍት አገልግሎት እንዲያገኝ ተደርጓል።

ከኮቪድ-19 ጋር ተያይዞ ቅድሚያ መከላከሉ እንዳለ ሆኖ በ2012 ዓ.ም ሲሰሩ የነበሩ ሥራዎችን የማስቀጠል የተሰሩ ሥራዎችን በሀገር አቀፍና ባለማቀፍ መድረኮች ላይ ማቅረብ ተችሏል።

እንዲሁም በምህንድስናው ዘርፋ ተመርቀው ስራ ያጡ ወጣቶችን ሀሳባቸውን ወደ ስራ እና ቢዝነስ እንዲቀይሩ በማድረግ ስንሰራ ቆይተናል። ከቡሬ አግሮ ኢንዱስትሪ እና ባሕር ዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር ታክስ ፎክስ አቋቁመን ለኢንዱስትሪ ትስስር የሚመጥን ሥራ ሥንሰራ ቆይተናል።

ያለንን ውስን ሀብት ከመጠቀም አንጻር በተወሰኑ የምርምር አጀንዳዎች በተለይ ግብርና፣ጤና፣ማህበረሰብ ሳይንስ፣ቴክኖሎጂ እና ቴክስታይል ላይ የተወሰኑ የትምህርት መስኮች መነሻ በማድረግ ሜጋ ፕሮጀክቶች በራሳቸው አደረጃጀት እንዲሰሩ ማድረግ ተሞክሯል።

በትብብር የምናመጣቸው ፕሮጀክቶች በትክክል ለታለመለት አላማ መዋላቸውን ጥብቅ ክትትል እናደርጋለን ይህም የራሱ አደረጃጀት አለው::: በትምህርት ፣ በፖለቲካል ሳይንስና በህግ ፣ እንዲሁም ከግብርና ጋር ተያይዞ በሰብል ልማት፣ በከብት መኖ፣ በከብት ማድለብ ስራ ላይ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን ከአውሮፓና ከጃፓን ትልልቅ ፕሮጀክቶች አጋርነት የሚሰሩትን ስራ ለማህበረሰቡ በትክክል የማድረስ ስራ እንሰራለን።

ናይል፡- በምርምር እና ማ/ሰብ አገልግሎት የስራ ሂደት በዓመቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው

ዶ/ር ተስፋዬ፡- በሂደቱ ካጋጥጠሙ ችግሮች መካከል ቁጥር አንድ የግዥ ስርዓቱ ነው እውነት ለመናገር ለምርምርና ለቴክኖሎጂ ሽግግር ትልቁ ማነቆ የግዥ ስርዓቱ ነው።

በጥቃቅን ምክንያቶች የፈለግነውን ያክል እንዳንሄድ አድርጎናል። በቴክኖሎጂ ሽግግሩ የአካባቢውን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ጥሩ ጥሩ ፕሮጀክቶች ነበሩ ግን የነሱን እቃዎች መግዛት የግዥ ሰራተኞች ጥሩ እያገዙን ቢሆንም በአቅራቢዎች በኩል ያለው ማነቆ በጣም ከባድ ነው።

ለወደፊት ግን እንደሀገር አጀንዳ ተይዞ በሀገር አቀፍ ደረጃ አቋም ተይዟል። ሁለተኛ በኮቪድ እና በሀገሪቱ የደህንነት ችግር ምክንያት መምህራን ከክልል ክልል ከወረዳ ወረዳ ተንቀሳቅሶ ምርምር ለመስራት ችግር ነበር። እንዲሁም ለምርምር የተጠቀሙበትን ገንዘብ በወቅቱ አወርርዶ ቀጣይ ስራን ለመስራት የሚወስደው ጊዜ አሰልች በመሆኑ መምህራን የምርምር ስራ ለመስራት በሚፈለገው መንገድ መሄድ አልቻሉም።

ናይል፡- በሂደቱ ያጋጠሙ ችግሮች ላይ የተወሰዱ እርምጃዎች/ መፍትሄዎች ካሉ

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲና አካባቢው የማህበረሰብ ራዲዮ ኤፍ ኤም 93.3 መደበኛ ስርጭቱን መጀመሩ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም በመደበኛ ፕሮግራሞቹ የተለያዩ አዝናኝ አስተማሪና ግንዛቤ የሚያስጨብጡ መሰናዶዎችን በየእለቱ ይዞላችሁ

ቀርቧል፡፡ ቆይታዎን በየእለቱ ከኤፍ ኤም 93.3 ጋር ካደረጉ

- ለሃገራችን ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ግለሰቦችን የሚዳስሰውን፡- **ዝክረ - ሰብ**
- በሳቅ እያዋዛ አስተማሪ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚያነሳውን፡- **ሳቅና ቁም ነገር**
- ማንኛውንም ሃሳብ ከህግ አንጻር የሚዳስሰውን፡- **ነገረ - ህግ**
- በግለሰቦች የግል ተሰጥኦ ላይ የሚያተኩረውን **መክሊት** መሰናዶ መከታተል ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም፡-

- ዝክረ - ታሪክ
- ዋልታና ማገሩ
- ወደራስ
- ካምፓስኛ
- የጥበብ ስፖርትና
- ዜና መጽሄት መሰናዶን ከተለያዩ መረጃዎች ጋር ያደርሳል፡፡

በመሆኑም በየእለቱ ከቀኑ 8 ሰአት እስከ 11 ሰአት ምርጫዎን የባህርዳር ዩኒቨርሲቲና አካባቢው የማህበረሰብ ራዲዮ ኤፍ ኤም 93.3 ን ያድርጉ፡፡

**ኤፍ ኤም 93.3**

**የጥበብ ድምጽ**

